B.N. Lapsley
2/9/96

# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

...SLEY / BROOKS FOUNDATION, INC.
... N. GREENVILLE AVE. ST. 610
...SON, TEXAS 75081, USA

**ከሉሌ መልአኩ**

**<u>አሳታሚ</u>፡ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት**

**አዲስ አበባ 1986 ዓ.ም**

# ማ ው ጫ

ገጽ
መግቢያ ........................................................ 7

## ክፍል አንድ

## ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ (እስከ 313 ዓ·ም)

ዘመነ ሐዋርያት (እስከ ሐዋርያው ዮሐንስ ዕረፍት ፤ 100 ዓ·ም) ........................................................ 12
ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች . 28
የስደት ዘመኖች (ዘመነ ሰማዕታት ፣ 64–313 ዓ·ም) ..... 33
ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መናፍቃንን በመቃወም ያደረገችው የመንፈስ ተጋድሎ ........................................ 37
የጥንት ክርስቲያኖች ሥርዓተ እምነት አፈጻጸም ........ 39
በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መቶ ዘመናት የቤተ ክርስቲያን አመራር ........................................................ 41
ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት የረዱ ..................... 42
የክርስትና ድል መንሣትና መስፋፋት ..................... 43
በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን መናፍቃንን ለመቃወም የተደረጉ ታላላቅ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) ........................................................ 45
በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን የተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ........................................ 49
በአራተኛው መቶ ዘመን የነበሩት አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓትርያርኮች) ........................................ 55

በኦርየንታል (በተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስ ፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ካሉት የሃይማኖትና የሥርዓት ልዩነቶች ጥቂቶቹ (ዋና ዋና ዎቹ) ........ 56

# ክፍል ሁለት

## የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

### ምዕራፍ ፩

የእስክንድርያ (የግብጽ ፣ የኮፕት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ 61

### ምዕራፍ ፪

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ 123

### ምዕራፍ ፫

የሶርያ (የአንጾኪያ ፣ ያዕቆባዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ 143

### ምዕራፍ ፬

በደቡብ ሕንድ የሐዋርያው ቶማስ (የማላባር ፣ የኬራላ) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ 152

### ምዕራፍ ፭

የአርመን (ጎርጎርዮሳዊት) ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ 157

## ክፍል ሦስት

## የምሥራቅ (የግሪክና የእስላቮኒክ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ታሪክ .................................................... 166

ምዕራፍ ፩

የቍስጥንጥንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .... 177

ምዕራፍ ፪

የእስክንድርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ...... 179

ምዕራፍ ፫

የአንጾኪያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .......... 180

ምዕራፍ ፬

የኢየሩሳሌም ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ...... 181

ምዕራፍ ፭

የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .............. 182

ምዕራፍ ፮

የሩማንያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........... 190

ምዕራፍ ፯

የሰርቢያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........... 191

ምዕራፍ ፰

የቡልጋርያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ......... 193

## ምዕራፍ ፱

የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ............. 195

## ምዕራፍ ፲

የቆጵሮስ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ .......... 197

# ክፍል አራት

## የምዕራብ (የካቶሊክና የፕሮቴስታንት) አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ

## ምዕራፍ ፩

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ......................... 200

## ምዕራፍ ፪

የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ .......... 258

# ክፍል አምስት

በ20ኛው መቶ ዘመን የተጀመረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ (ጉባኤ ፣ ማኅበር) ............................................ 311

የክርስትናን እምነት የሚከተሉ ምእመናን ቍጥር ግምት ............................................ 326

# መግቢያ

ከዚህ በታች መጽሐፉን ስላዘጋጀሁበት ምክንያትና ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አጠቃላይ መግቢያ (መግለጫ) እጽፋለሁ ።

ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ የተነሣሣሁት ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የአምስቱን የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ሳስተምር መጠነኛ ዝግጅት ስላደረግሁ ነው ። ይህም ዝግጅት የተሟላ ባይሆንም ቅሉ ፡ ካህናትና ምእመናን በእምነት አንድ ስለሆንነው የኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ አጠቃላይ ዕውቀትና ግንዛቤ እንዲያገኙ በማለት ታሪኩ በትንሣኤ መጽሔት እየታተመ በተከታታይ በመውጣት ላይ ነው ። ሆኖም በመጽሔት እያሳተሙ ማውጣቱ ብዙ ጊዜ ስለሚፈጅ ከኦርየንታል አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ጋር የቤተ ክርስቲያንን በክርስቶስ መመሥረት ፡ የግሪክ ኦርቶዶክስን ፥ የካቶሊክን ፡ የፕሮቴስታንትንና በሃያኛው መቶ ዘመን የተጀመረውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ንቅናቄ (ጉባኤ ፥ ማኅበር) በአምስት ክፍሎች አዘጋጅቼ ሁሉንም "የቤተ ክርስቲያን ታሪክ" በሚል ርእስ አቅርቤአለሁ ።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ለወደፊት ብዙ መጻሕፍትን በመመል ከትና ከሊቃውንት በመጠየቅ በቀጣዩ እትም ተሻሽሎ እንደሚወጣ ተስፋ አደርጋለሁ ። ሆኖም መጽሐፉን የሚያነቡ ሁሉ ለወደፊት ተሻሽሎ በሚታተምበት ጊዜ ለማስተካከል የሚያስችል ገምቢ አስተያየት እንዲለ ግሱኝ በትሕትና እጠይቃለሁ ።

መጽሐፉን ሳዘጋጅ የተጠቀምሁባቸው አብዛኛዎቹ መጻሕፍት በውጭ ሀገር ቋንቋ የተጻፉ ስለሆኑ ዓመተ ምሕረቶች የተጻፉት እንደ አውሮጳ አቈጣጠር ነው ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ያሉት ዓመተ ምሕረቶች ግን እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ተጽፈዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ እንደፈተኞቹ መጻሕፍቶቼ ሁሉ አሁንም ይህን መጽሐፍ መርም ሮና የጐደለውን አሟልቶ ለሕትመት እንዲበቃ ስላደረገልኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ። ምናልባት በመጽሐፉ ውስጥ ስሕተት መስሎ የሚታይ ቢገኝ የሚመለከት እኔን ነው ። እንዲሁም ይህን መጽሐፍ አዘጋጅቶ

እንዳሳትም በሐሳብ የረዱኝንና ያበረታቱኝን ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/አማኑኤልን አመሰግናለሁ ። በመጨረሻም መጽሐፉ ለካህናትና ለምእመናን ጠቃሚ ሆኖ እንደሚገኝ እምናለሁ ።

እዚህ ድረስ መጽሐፉን ለማዘጋጀት የተነሣሣሁበትን ምክንያት ተመለከትን ። ቀጣዩ ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚገልጸው አጠር ያለ መግቢያ ነው ።

ሀ) <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ። ሕፃን ሽማግሌ ፣ ድኻ ሀብታም ፣ ወንድ ሴት ፣ የተማረ ያልተማረ በመባባል ሳንለያይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ" (ማቴ· 18፡20) ብሎ ባስተማረው መሠረት ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት ፣ በአንድነት ፈጣሪያችንን ለማምለክ የምንሰበሰብበት ቅዱስ ቦታ ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት መሆኑን የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ ።

ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጀትና ራሷ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ፡ መሪዋና አጽናኟ መንፈስ ቅዱስ ነው (የሐዋ· 20፡28 ፤ 9፡31 ፤ ኤፌ· 5፡ 26 ፡ ቆላ· 1፡18)።

ክርስትና ከተመሠረተች ጀምሮ ክርስቲያኖች በየቤቱና በየዋሻው እየተሰበሰቡ ለፈጣሪያችን ምስጋና ሲያቀርቡ ከቈዩ በኋላ መጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ የተሠራ ፊልጵስዩስ በሚባለው ሀገር ነው ።

ለ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> ። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ መንፈሳዊት ዓለም ስለሆነች ፡ የተለየ ታሪክ አላት ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፡ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ መሠረትነት ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመናችን ድረስ ያለውን ታሪኳን ፡ እንደምን እንደተመሠረተች ፡ እንደምን የዓለም ሕዝብ እንደተቀበላት ፣ በየጊዜው ከአባላቷና ከተቃዋሚዎቿ የተሰነዘሩባትን የኑፋቄ ትምህርቶችና ስደቶች በጸና ሃይማኖት በመቋቋም (በመጋደል) እንደምን እንዳሳለፈቻቸው ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንዳስፋፋችና ይህንንም የመሳሰለውን ሁሉ ያስተምረናል ።

ሐ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች (መገኛዎች)</u> ።

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በዝርዝር ለማጥናት የሚፈልግ ሰው ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች የሆኑትን ልዩ ልዩ መጻሕፍት መመልከት ይገባዋል ። እነሱም የሚቀጥሉት ናቸው ።

1ኛ/ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ። 2ኛ/ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው መጻሕፍት ። በየጊዜው በተደረጉት ጉባኤዎች የተወሰኑትና ነገሥታት ስለ ቤተ ክርስቲያን የደነገጓቸው ሕጎች ናቸው ። 3ኛ/ ታሪኩ በተፈጸመበት ቦታ ተገኝተውና ዘመን ኖረው የቤተክርስቲያንና የውጭ ታሪክ ጸሐፊዎች የጻፏቸው መጻሕፍት ናቸው ። 4ኛ/ በየጊዜው የተገኙ ትና የሚገኙት የክርስቲያኖች መቃብር ፣ መቅደሶች ፣ ሥዕሎች ፣ ገንዘቦች፣ ጽሑፎችና እነዚህን የመሳሰሉት የአርኬዎሎጂ (የጥንታውያን ነገሮች ምርመራ) ቅርሶች ናቸው ።

መ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አከፋፈል</u> ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሦስት ክፍሎች ይከፈላል ።

1ኛ/ መጀመሪያው ፣ የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ። ጌታ ቤተ ክርስቲያንን በሐዋርያት ላይ ከመሠረተበት ዘመን ጀምሮ እስከ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ ድረስ ነው (እስከ 313 ዓ·ም) ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሮማ መንግሥት እስከ ወደቀበት እስከ 476 ዓ·ም ድረስ ነውም ይላሉ ።

2ኛ/ ሁለተኛው ፣ የመካከለኛው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ። ከትልቁ ቈስጠንጢኖስ ጀምሮ ቍስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ እስከ ወደቀች በት ጊዜ ድረስ ነው (313—1453 ዓ·ም) ።

3ኛ/ ሦስተኛው ፣ አዲሱ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል ። ቍስጥንጥንያ በቱርኮች እጅ ከወደቀችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ ነው (1453—1993 |1986| ዓ.ም) ።

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች በየራሳቸው እምነት ላይ ታላላቅ ድርጊቶች የተፈጸሙባቸውን ዘመናት መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በተለያዩ ጊዜዎች ይከፍሉታል ።

በዚህ መጽሐፍ የተከተልሁት አከፋፈል ከላይኛው ለየት ያለ ነው ። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ (451 ዓ·ም) ያለው ታሪክ በክፍል አንድ ተገልጿል ። እስከ አምስተኛው መቶ ዘመን ድረስ በእምነት አንድ የነበረችዪቱ ቤተ ክርስቲያን በኬልቄዶን ጉባኤ ከተለያየች በኋላ ተለያይተው የሚኖሩትና በሃያኛው መቶ ዘመን የተጀመረው የዓለም

አብያተ ክርስቲያናት ንቅናቄ (ማኅበር ፣ ጉባኤ) ታሪክ ከሁለት እስከ አምስት ባሉት ክፍሎች ውስጥ ተጽፏል ።

ሠ) <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጠቃሚነት</u> ። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከዓለም ታሪክ አንደኛውን ክፍል ይዞ ስለሚገኝ ፣ የሕዝቦችን የሥልጣኔ እርምጃና ታሪክ ለማጥናት ለሚፈልግ ሰው ሁሉ በጣም ጠቃሚ ነው ። በተለይ ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ በሚያጠና በት ጊዜ የእምነቱን ታሪክ ፣ እንዲሁም አባቶቻችን በየጊዜው ባስተማሩት መንፈሳዊ ትምህርት የሕዝቡ ጠባይ እንዴት እንደ ተሻሻለ ለማወቅና ራሱንና ምእመናንን በእግዚአብሔር መንገድ ለመምራት ይችላል ። ከዚህም በስተቀር የቤተ ክርስቲያንን ከፍተኛነትና ጠቃሚነት ለመገንዘብና ለምእመናንም ለማስገንዘብ እንዲችል ይረዳዋል ።

ረ) <u>ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የነበረው የዓለም ሕዝብ አምልኮና አኳኋን</u> ። ክርስትና ለዓለም ሕዝብ ያስገኘችውን ከፍ ያለ ጥቅም ለመረዳት ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የነበረውን ሕዝብ አምልኮና ጠባይ ከዚህ በታች ባጭሩ እንመልከት ።

በዚያን ዘመን ምንም እንኳ የዓለም ገዥ የነበረው የሮም መንግሥት በኃይሉ ፣ በዕውቀቱ ፣ በሥልጣኔው ፣ በሀብቱና በማንኛውም ነገር ዝናው በዓለም የታወቀና የገነነ ቢሆንም ፣ የአምልኮውና የግብረ ገብነቱ አኳኋን እጅግ በጣም አሳዛኝና የተበላሸ ዝቅተኛ ግምት የተሰጠው ነበር ። ሐዋርያው ጳውሎስ "የማይጠፋውንም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ" (ሮሜ 1፥23—25) ብሎ እንዳስተማረው ሁሉ ሕዝቡ ፍጡራን የሆኑ ብዙ ዓይነት ጣዖታትን ያመልኩ ነበር ። እንዲሁም ብዙዎችን ሰዎች ለሰው ልጅ የሚገባውን ነጻነት ነፍገው በባርነት ያሁቀዩአቸውና ባሮች ናችሁ በማለት እንደ ዕቃ ይመለከቷቸው ነበር ። ሴትም ነጻነቷን ተገፋ በቤቷ እንደ ቤተሰብ ነበረች ።

በዚያ የዓለም ሕዝብ ጣዖት በሚያመልክበት ዘመን በእግዚአብሔር ያመልክ የነበረው የእስራኤል ሕዝብና የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነበር።

ምንም እንኳ ከአይሁድ መካከል ጥቂቶቹ ፍጹም እምነት ስለነበራቸው ፣ የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣት ቢጠባበቁ (ዮሐ· 1፥46 ፣ ሉ·ቃ· 2፥25 32) ብዙዎቹ ግን የተሳሳተ እምነትን በመከተል በነቢያት

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው ትንቢት ስለ ምድራዊ ገዥ ነው አሉ።

ጸሐፍትና ፈሪሳውያንም ይፈጽሙት የነበረው አምልኮ ለመታየትና ውዳሴ ከንቱን በመሻት ነበር እንጂ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር ከልብ የመነጨ አልነበረም። ከአይሁድ መካከል ፈሪሳውያን ትንሣኤ ሙታን መኖሩን ሲያምኑ ፣ ሰዱቃውያን አያምኑም ነበር (ማቴ·22፡23)።

ያን ጊዜ በአይሁድና በሳምራውያን መካከል ታላቅ ጠብ ነበረ። ምክንያቱም ሰማርያ የሚኖሩ አይሁድ በምርኮ ምክንያት ከአሕዛብ ጋር በጋብቻ ተቀላቅለው ስለነበረ ፣ ከብሉይ ኪዳንም መጀመሪያዎችን አምስቱን የሙሴን መጻሕፍት ብቻ ስለተቀበሉና ኢየሩሳሌም ወደ ነበረው ቤተ መቅደስ ሄደው አምላካቸውን በማምለክ ፈንታ ገሪዛን በተባለው ተራራ ላይ የራሳቸውን ቤተ መቅደስ ሠርተው እግዚአብሔርን ስላመለኩ ፣ እንዲሁም አንዳንዶቹ ጣዖትንም ስላመለኩ አይሁድ በጣም ይጠሏቸው ነበር (ዮሐ· 4፡9)።

የዚህ ዓለም ሕዝብ ከላይ እንደተመለከትነው ባለ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ወድቆ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምን ልጆች ከወደቅንበት ኃጢአት በደሙ ለማዳን መጥቶ በሰው ልጆች መካከል ልዩነት የማታደርግ የሰውን መንፈስ ጥም የምታረካና ከእግዚአብሔር ልጅነት የምታስጥ እውነተኛይቱን የክርስትናን ሃይማኖት መሠረተልን።

ሉሌ መልአኩ

# ክፍል አንድ

## ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ትልቁ ቈስጠንጢኖስ (እስከ 313 ዓ.ም)

### ዘመነ ሐዋርያት (እስከ ሐዋርያው ዮሐንስ ዕረፍት ፣ 100 ዓ.ም)
### ከልደት እስከ ጰንጠቆስጤ
### ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጀምሮ እስከ ጰንጠቆስጤ ድረስ የተፈጸሙ ሥራዎች

ሐዋርያው ጳውሎስ "ጊዜውም በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ..." (ገላ. 4፡4) እንደሚለው ሁሉ እግዚአብሔር ለአባታችን ለአዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከወደቅንበት ኃጢአት ለማዳን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ቤተልሔም ተወለደ ። ለእናቱና ለዘመዶቹም እየታዘዘ አደገ (ሉቃ. 2፡51)።

በሠላሳ ዓመቱ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ ። የባሕርይ ልጅነቱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ አስመሰከረ ። ከዚያ ቀጥሎ 40 መዓልት፣ 40 ሌሊት ከጾመ በኋላ በኢየሩሳሌም ማስተማር ጀመረ ። ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያትና ሰባ ሁለቱን አርድእት መረጠ ። በመዋዕለ ስብከቱም ልዩ ልዩ የሆኑ ታምራትን በማድረግ ድውያንን ፈወሰ ። ሙታንን አስነሣ ። የአይሁድ ካህናት ግን የሚያደርጋቸውን ታምራት አይተው የሚያስተምረውን ትምህርት ሰምተው በማመን ፈንታ ተቃወሙት ። የሕዝቡም ጠባይ ግልብጥብጥ ስለነበረ አንዳንድ ጊዜ የጌታን ሥራ ሲያደንቅ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ይቃወም ነበር ። ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ካስተማረ በኋላ የሆሣዕና ዕለት በሕዝቡ ታጅቦ በምስጋና ወደ ኢየሩሳሌም ገባ (ማቴ. 21፡9) ። የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ከሊቀ ካህናት በተላኩት ወታደሮች በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ ውስጥ በተያዘ ጊዜ ጴጥሮስና

ዮሐንስ ሲቀሩ የቀሩት ሐዋርያት ጥለውት ተበተኑ (ማቴ· 26፥56)። ከሁሉቱም ጌታ እስከ ተሰቀለበት ጊዜ የቈየ ዮሐንስ ብቻ ስለነበረ ፤ እዚያው እመስቀሉ ሥር ሳለ እመቤታችንን እንዲረዳት ከጌታ አደራ ተቀበለ (ዮሐ·19፥26) ።

ጌታ በተሰቀለ ጊዜ የተደረጉት ታምራት ሐዋርያትን ሊያደፋፍሩአቸው ቻሉ ። የሐዋርያትን ኃዘንና ጭንቀት ወደ ደስታ ፣ ፍርሃታቸውን ወደ ድፍረት ፣ ተስፋ መቍረጣቸውን ተስፋ ወደ ማድረግ የለወጠው የጌታ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ መነሣት ነው ። ከመቃብር ከተነሣ በኋላ በዚህ ዓለም አርባ ቀኖች ቈየ ። በነዚህ ቀኖች ውስጥ ለሐዋርያት በገሊላና በኢየሩሳሌም እየተገለጸ ምሥጢራትን እየፈጸመ የሐዋርያነት ሥራቸውን እንዴት እንደሚሠሩ ሲያስረዳቸው ከሰነበተ በኋላ ዐረገ ።

መቶ ሃያ የሚሆኑ ደቀ መዛሙርት ተሰብስበው ሳለ ጴጥሮስ ጌታን በካደው በይሁዳ ፈንታ ሌላ ሐዋርያ እንዲተካ ጠየቀ ። በሐሳቡ ሁሉም ስለተስማሙ ፣ ፍጹሙን እንዲመርጥ ወደ እግዚአብሔር ከጸለዩ በኋላ ለኢዮስጦስና ለማትያስ ዕጣ ቢጥሉ ፣ ዕጣው ለማትያስ ስለወጣለት ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ (የሐዋ· 1፥26) ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ካህናት በጣም ታላቅ ለሆነው መንፈሳዊ ሥራቸው በጸሎት በአንብሮተ እድ የሚሾሙ ሆነዋል ።

## ጌታ ከሙታን በተነሣ በኀምሳኛው ቀን (የጰንጠቆስጤ ፣ የጰራቅሊጦስ ዕለት) የመንፈስ ቅዱስ መውረድና የመጀመሪያ ዪቱ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

እስከ ጰንጠቆስጤ ድረስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት ተስፋውን ሲጠባበቁ ቈይተው ጌታ በዐረገ በዐሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ተሰጣቸው ። ሐዋርያትም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የእግዚአብሔርን ክብር ይናገሩ ጀመር ። በዚያን ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ስብከት አደረገ ። የተሰበሰበውም ሕዝብ ልብ በስብከቱ ስለተነካ ሦስት ሺህ የሚሆኑ ክርስትናን ተቀብለው ተጠመቁ ። በሐዋርያትና በነዚህ በተጠመቁት መጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች (የሐዋ· 2፥41 ፤ ኤፌ· 2፥20 ፤ ራእ· 21፥14)።

የጰንጠቆስጤ ዕለት ካመኑት አይሁድ መካከል አብዛኞዎቹ ከፍልስጥኤም ውጭ በየሀገሩ ተሰደው የሚኖሩ ስለነበሩ ፣ የበዓሉ ጊዜ ሲያልቅ

ወደየመጡበት ሀገር ተመልሰው የክርስትናን ትምህርት ላልሰማው ሕዝብ ስላሰሙ ፣ ከፍልስጥኤም ውጭ የወንጌል መልእክተኞችና የቤተ ክርስቲያን መሥራቾች ሆኑ ። ያን ጊዜ በወረደው መንፈስ ቅዱስ ኃይል በጥቂት ጊዜ ውስጥ የጣዖት አምልኮና የተሳሳቱ እምነቶች ሁሉ ሊጠፉና በክርስትና የዓለም መልክ ሊለወጥ ቻለ ። መንፈስ ቅዱስ ለዘለዓለም በቤተ ክርስቲያን ላይ አድሮ ይኖራል ። ከስሕተት ጎዳና ጠብቆ ወደ እውነት ይመራታል ። የእውነተኛዎችንም ክርስቲያኖች ልብ ከዚህ በፊት በመንፈሳዊ ቅናት መልቶት ነበር ። ለወደፊትም ይመላዋል ።

## ሐዋርያት ያደረጉአቸው መጀመሪያዎች ታምራትና ከአይሁድ የደረሱባቸው ስደቶች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ልዩ ልዩ ታምራት እንደሚያደርጉ አስቀድሞ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል ፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ ፤ … እጆቻውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ ፤ እነሱም ይድናሉ" (ማር. 16፡17–18) ሲል ባስተማረው መሠረት ከጰንጠቆስጤ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለጸሎት ወደ ምኩራብ ሲሄዱ ሲወለድ ጀምሮ አንካሳ የነበረውን ሰው ጴጥሮስ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ሥልጣን ፈወሰው ። የአይሁድ ካህናት ጴጥሮስ ያደረገውን ታምርና ስብከት በመስማት ተናደው ጴጥሮስንና ዮሐንስን አሰሩአቸው ። ዳግመኛም በኢየሱስ ስም እንዳያስተምሩና ታምራት እንዳይሠሩ በዛቻ አስፈራር ተው ፈቷቸው ። ሐዋርያትም ዛቻውን ከጉዳይ ሳይጽፉ ያስተምሩና ታምራት ያደርጉ ጀመር ። ያደረጉአቸውም ታምራት በመላ ፍልስጥኤም ስለተሰሙ በሽተኞች ሁሉ ለመዳን ሐዋርያት ወደአሉበት በብዛት ይጐርፉ ነበር ። የሃይማኖት ኃላፊዎች የነበሩት አይሁድም ይህንን ወሬ ሰምተው በጣም ስለተሸበሩ ሐዋርያት ተይዘው ለፍርድ እንዲቀርቡ አዘዙ። የካህናት አለቃው ስለ ኢየሱስ እንዳያስተምሩ በማለት የሰጣቸ ውን ትእዛዝ ባለመፈጸማቸው ዘለፋቸው ። ያን ጊዜ ጴጥሮስ በታላቅ ድፍረት ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል ። ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር የሚያግደን ማንም የለ በማለት መልስ ስለሰጠ ሊቀ ካህናቱና ፈራጆቹ በጣም ተበሳጩ ።

የሕግ አስተማሪና በሕዝቡም ፊት ክብር የነበረው ገማልያል

ለፈራጆቹ መልካም ምክሩን እንዲህ ሲል አቀረበ "… ተውአቸው ፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና ፤ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም ፤ በእርግጥ ከእግዚአብ ሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ" (የሐዋ· 5፥38–39) ። ስለዚህ የገማልያል ንግግር ፈራጆችን ስለአስታገሣቸው ለማስፈራሪያ ያህል ሐዋርያት ተገርፈው ተለቀቁ ። እነሱም "ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአ ችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ ። ደስ ይበላችሁ ። ዋጋችሁ በሰማያት ብዙ ነውና ። … (ማቴ· 5፥ 11–12) ብሎ ጌታ ያስተማረውን በማሰብ የተቀደሰ ሥራቸውን በበለጠ ደስታ ቀጠሉ ። ቀስ በቀስም የክርስቲያኖች ቊጥር ከሴቶችና ከልጆች በስተቀር 5ሺህ ያህል ሆነ (የሐዋ. 4፥4) ።

## የመጀመሪያዎች ክርስቲያኖች ሕይወት

በኢየሩሳሌም ውስጥ በተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ሥር የነበሩት ክርስቲያኖች ከሰዓት በኋላ ጊዜ ወስነው በኢየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ በያዕቆብ ፥ በማርቆስ እናት በማርያም ቤትና እነዚህን በመሳሰሉ ቤቶች እየተሰበሰቡ የሐዋርያትን ትምህርት ይሰሙ ነበር (የሐዋ· 12፥ 12)። በስብሰባውም ጊዜ የወንጌልን ትምህርት በተለይም የክርስቶስን ትንሣኤ በዐይናቸው ያዩ መሆናቸውን እያረጋገጡ ያስተምሩአቸው ነበር። ከዚህም በስተቀር ከብሉይ ኪዳን ስለ መሲሕ የሚናገሩት ትንቢቶች በኢየሱስ ክርስቶስ መፈጸማቸውን አስፋፍተው ያስረዱአቸው ነበር ። እንዲሁም በየጊዜው ሥጋውን ደሙን በአንድነት እየተቀበሉ አንድነታቸውን አጽንተው ይኖሩ ነበር ። ደግሞ በወንድማማችነት መንፈስ የተሳሰሩ መሆናቸውን በመግለጽ በአንድነት በአንድ ማዕድ ላይ ተቀምጠው ይበሉ ነበር ። እነዚህም አገልግሎቶች የሚፈጸሙበት ቀን እሑድ ነበር ። ማንኛውም ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን የሚችለው ኃጢአቱን ተናዞ ተጠምቆ ሐዋርያት እጃቸውን በመጫን መንፈስ ቅዱስን ከአሳደሩበት በኋላ ነበር ። በምእመናን ሁሉ ዘንድ መንፈሳዊ ደስታ ፥ ትሕትና ፥ ፍቅርና እነዚህን የመሳሰሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ጐልተው ይታዩ ነበር ። ከእነሱም መካከል የማስተ ማር፥ ትንቢት የመናገር ፥ ታምራት የመሥራት ኃይል የተሰጣቸው ነበሩ (የሐዋ· 11፥28) ።

ከክርስትና እምነት ውጭ የነበረው ሕዝብ በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ የተደረገውን ታላቅ ለውጥ በማየት ወደ ክርስትና እምነት በብዛት ስለመጣ የክርስቲያኖች ቍጥር እየበዛ ሄደ ። በዚያን ጊዜ የነበሩ ክርስቲያኖች ከመካከላቸው ችግርን ለማስወገድ በማሰብ እየተሰበሰቡ ገንዘብ በማዋጣት መከራና ችግር የደረሰባቸውን ሁሉ በሚገባ ይረዱአ ቸው ነበር ። ሀብታሞች ያለአንዳች አስገዳጅ በወንድምነት ፍቅር ተስበው በፈቃዳቸው ርስታቸውን እየሸጡ ለድኾች እንዲያካፍሉላቸው ለሐዋርያት ይሰጡ ነበር ። እንደዚህ ያለውን ርዳታ ካደረጉት መጀመሪ ያው ሰው ከቆጵሮስ የሄደው አይሁዳዊው በርናባስ (ዮሴፍ) ነበር (የሐዋ· 2፡42–47 ፤ 4፡ 32–37) ።

ሐዋርያው ጳውሎስም በንፍገት መንፈስ በመመራት ወንድሞቻ ቸው ሲራቡ እያዩ ባለማዘን ብቻቸውን የሚበሉትን "በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት ይበላልና ፤ አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል …" (1ቆሮ· 11፡21–22) በማለት በማኅበር ከድኾች ጋር አብረው እንዲበሉ የሰጠው ምክር በዚሁ መሠረት ነው ።

አይሁድ ክርስቲያኖችን ገሊላውያን ፣ ናዝራውያን ይሏቸው ነበር ። ክርስቲያኖች ግን ወንድሞች ፣ ደቀ መዛሙርት እየተባሉ ይጠሩ ነበር (የሐዋ· 1፡15 ፤ 6፡1)። ክርስቲያን መባል ግን በኋላ በአንጾኪያ የተጀመረ ነው ። ይህንንም ክርስቲያን የሚለውን ስም የአንጾኪያ ሰዎች ያወጡላ ቸው ክርስቶስ የተባለውን በማምለካቸው ሲያፌዙባቸው ነበር (የሐዋ· 11፡26) ።

## የሰባቱ ዲያቆናት ምርጫ

የክርስቲያኖች ቍጥር በየጊዜው እየበዛ ስለሄደ በአንድነቱ ሥራ ውስጥ ሥራውን ተግተው አክብረው የሚፈጽሙ ግብረ ገቦችና ሥራ የማይወዱ ሰነፎች ተገኙ ። በዚህ ምክንያት በአንድነቱ ውስጥ መነቃቀፍ ተጀመረ ። ሐዋርያትም ይህን ሰምተው እንደዚህ ያለውን መነቃቀፍ ለማስቀረት ሲሉ ክርስቲያኖችን ሁሉ ሰብስበው የኛ ዋና ዓላማ ሕዝቡን ማስተማር ስለሆነ ተማከሩና ለዚህ ሥራ የሚሆኑ ጥበብን የተመሉ የጋለ መንፈሳዊ ቅናት ያላቸው ፣ በሕዝብ ዘንድ የተወደዱና መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰባት ሰዎች ምረጡ አሏቸው ። ሰባቱም በሕዝብ ድምፅ

ከተመረጡ በኋላ ሐዋርያት እጃቸውን ጭነው በጸሎት ሾሟቸው ። ከተመረጡ በኋላ ተባብረው ስለሠሩ የወንጌል ስብከት እየተስፋፋ ምእመናን እየበዙ ሄዱ ። ከአሪት ካህናትም ብዙዎች አመኑ (የሐዋ· 6፡2–7)። ለእነዚህ እንዲረዱአቸው በሐዋርያት ጥያቄ ለተመረጡት 7 ሰዎች ቤተ ክርስቲያን የክህነትን ማዕርግ በመስጠት ዲያቆናት (ረዳቶች ፥ አገልጋዮች) ብላ ሰየመቻቸው ።

## እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት

እስጢፋኖስ ፍጹም እምነት ፥ የጋለ መንፈሳዊ ቅናትና ታምር የማድረግ ጸጋ ነበረው ። ከተሰጠው ሥራም በስተቀር ጊዜ ባጋጠመው ቍጥር በየምኵራቡ እየዞረ ለአይሁድ ዓለምን ለማዳን ስለመጣው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሰ አስረዳቸው ። እሱም የሚናገረው በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ስለ ነበር ፥ በመቃወም ይከራከሩት የነበሩትን መልስ ስላሳጣቸው በቅናት መንፈስ በመመራት እሱን ለማጥፋት የሙሴን ሕግ ይነቅፋል ፥ እግዚአብሔርን ይሰድባል ብለው የሐሰት ምስክሮች አስነሡበት ። ይህም የሐሰት ወሬ በሕዝቡ ዘንድ ስለተነዛ እውነት መስሎ ታየ ። አንድ ቀን አይሁድ በቅናት መንፈስ በመመራት እስጢፋኖስን ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ይዘው ወደሸንጎ ወሰዱት ።

ቀደም ብለው የተሰናዱት የሐሰት ምስክሮችም "ይህ ሰው አሪትንና ቤተ መቅደስን ይነቅፋል ፤ በዚህ በተቀደሰው ስፍራ በሕግም ላይ የስድብን ነገር ለመናገር አይተውም ፤ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ቤተመቅደስ ያፈርሰዋል ፤ ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋል" ብለው መሰከሩበት (የሐዋ· 6፡13–14)።

በዚያን ጊዜ የእስጢፋኖስ ፊት እንደ መልአክ ፊት ሲያበራ አዩት ። የካህናት አለቃው መልስ እንዲሰጥ ቢጠይቀው ስለተከሰሰበት በመመለስ ፈንታ ፥ አይሁድ ከጥንት ጀምረው እግዚአብሔርን በመቃወም ስለሚያደርጉት መጥፎ ሥራ የተሰማውን ኃዘን ለመግለጽ ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ እስከ መድኃኒታችን ኢየሱስ ድረስ ያለውን የቅዱሳት መጻሕፍትን ጽሑፍ በሚገባ ተረከላቸው ። ይኸውም አይሁድ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕገ አሪትን ትተው ሞሎክ የተባለውን ጣዖት አመለኩ ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ መወለድ ትንቢት የተናገሩትን ነቢያት

ገደሉ ። ጌታንም በግፍ ሰቀሉ በማለት ገልጾ ነገራቸው ። አይሁድ የእስጢፋኖስን ንግግር ከሰሙ በኋላ እሱን በመቃወም በታላቅ ቁጣ ተሞሉ ። ጥርሳቸውንም አፋጩ ። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር ፥ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር አብ ዕሪና ተቀምጦ አየ ። እስጢፋኖስም የተገለጠለትን ምሥጢር በዙሪያው ለተሰበሰበው ሕዝብ በመግለጥ እንዲህ ሲል ተናገረ ። "እነሆ ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጦ አያለሁ" (የሐዋ·7፥56) ። አይሁድ እነዚህን ንግግሮች በእግዚአብሔር ላይ እንደተሰነዘሩ ስድቦች በመቍጠር ያለፍርድ ቤት ውሳኔ ዘለው ያዙት ። ከከተማም አውጥተው በድንጋይ ወግረው ገደሉት ። ወጋሪዎች ሲወግሩት ልብሶቻቸው እጆቻቸውን በመያዝ ግራ እንዳያጋቡአቸው ለማቃለል በማሰብ በዚያን ጊዜ የክርስትና አሳዳጅ የነበረው ሳውል ልብሶቻቸውን ይጠብቅላቸው ነበር ። የሚወረወሩት ድንጋዮችም እንደ ክረምት በረዶ በላዩ ላይ ሲወርዱበት ተንበርክኮ እንዲህ ሲል ጸለየላቸው ፥ "ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው" (የሐዋ· 7፥60)። እነዚህን ቃላት ከተናገረ በኋላ ዐረፈ። ደጋግ የሆኑ ክርስቲያኖች በድኑን ወስደው እንባ በእንባ እየተራጩ ቀበሩት ። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም በስሙ ቤተ ክርስቲያን አሳንፃ በዓሉን ጥር 1 ቀን ታከብራለች ።

በዚያን ጊዜ አይሁድ ክርስትናን እናጠፋለን ብለው ባነሡት ስደት ምክንያት ከሐዋርያት በስተቀር ወደ ሰማርያ ፥ ፊኒቅያ ፥ ቆጵሮስና ሶርያ (አንጾኪያ) የተሰደዱት ክርስቲያኖች ሁሉ በየሄዱበት ሀገር ስላስተማሩ ፥ ይህ ስደት ክርስቲያኖችን በማጥፋት ፈንታ ለክርስትና መስፋፋት በጣም ጠቀመ ።

## ፊልጶስ

ከእስጢፋኖስ ዕረፍት በኋላ ከአይሁድ በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ስደት ምክንያት ኢየሩሳሌምን ለቀው ከተሰደዱት አንዱ ፊልጶስ ነበር ። የእርሱም ከኢየሩሳሌም መራቅ ወንጌልን ከኢየሩሳሌም ውጭ እንዲያስተምር ምክንያት ሆነው ። በሰማርያ ውስጥ አስተምሮና ታምራት አድርጎ ብዙ ሰዎችን አጠመቀ ። በጥንቈላ ሥራው ሰዎችን ያታልል የነበረው ጠንቋዩ ሲሞንም በክርስቶስ አምኖ ተጠመቀ ። ሐዋርያትም የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ በሰሙ ጊዜ ፥ ከኢየሩሳሌም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ሰማርያ ሄደው በተጠመቁት ላይ

እጃቸውን በመጫን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ሲያሳድሩባቸው ሲሞን ስላየ እንደነርሱ ያለ ሥልጣን እንዲኖረው ፈለገ ። ወዲያውም ብዙ ገንዘብ በሐዋርያት ፊት አቅርቦ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን የማሳደር ሥልጣን ለእርሱም እንዲሸጡለት ልመናውን አቀረበ ። ጴጥሮስም ጥያቄውን በመቃወምና እምነተ ቢስነቱን በመግለጽ የእግዚአብሔር ስጦታ በገን ዘብ ይገዛል ብለህ ማሰብህ በጣም ታላቅ ጥፋት ነው አለው ። ሲሞንም ከዚያች ጊዜ ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት ተወገደ ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ማዕርገ ክህነት ለማግኘት ጉቦ የሚሰጡና ለመስጠትም የሚቀበሉ ሁሉ ሲሞናውያን ተብለው ይጠሩ ጀመር ። እንደዚህ ያለውን አጉል ሥራ ሲፈጽሙ የሚገኙ ሁሉ ማዕርገ ክህነታቸውን ይገፈፋሉ ። ከዚህ በኋላ ሲሞን በውጪ ክርስቲያን መስሎ እየታየ ውስጥ ውስጡን የክርስትናን እምነት በመቃወም በሰማርያ ሰዎች ዘንድ ይሰብከው የነበረውን የተሳሳተ ሐሳቡን በክርስቲያኖች ዘንድ መንዛት ስለጀመረ የመጀመሪያው ከሐዲና የከሐዲዎች መሪ የሚል ስም ተሰጠው ።

ጴጥሮስና ዮሐንስ ሥራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ሰማርያ በሚገኙት መንደሮች እየሰበኩ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ ። ፊልጶስም ከሰማርያ ወደ ጋዛ እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ ስለአዘዘው ሄደ ። በዚያም መንገድ አንድ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለ ሥልጣን ኢየሩሳሌም ሄዶ በዓል አክብሮ ወደ ሀገሩ በመመለስ ላይ ሳለ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ የኢሳይያስን መጽሐፍ ገልጦ ዓለምን ለማዳን ስለመጣው መሲሕ ሕማም ፣ ሞትና ትንሣኤ የሚናገሩትን ትንቢቶች (ኢሳ 53፡7) እያሰማ ሲያነብ ፊልጶስ ሰምቶ የምታነበውን ታውቀዋለህን አለው ። ጃንደረባውም ያስተማረኝ ሳይኖር በምን አውቀዋለሁ ፤ ነቢዩ ይህን የተናገረ ስለራሱ ነው? ወይስ ስለ ሌላ እባክህ አስረዳኝ አለው ፤ በሠረገላውም ላይ አስቀመጠው ፤ እንዲህ ሲል ተረጐመለት ፣ ይህ የኢሳይያስ ትንቢት በአይሁድ እጅ በተሰቀለውና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ በተነሣው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንደተፈጸመ ገለጸለት ። ይህንንም እየተነጋገሩ ሲሄዱ ከውኃ ደረሱ ፣ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምኖ ተጠመቀ ። ፊልጶስም ከአጠመቀው በኋላ ከፊቱ ተሰወረ ። በዚህ አኳኋን በአፍሪካ አሕጉር ክርስትናን በመቀበል መጀመሪያ የሆነው ይህ ኢትዮጵያዊ መኰንን የክርስትናን እምነትና ትምህርት ወደ ሀገራችን

አመጣልን (የሐዋ·8፡ 27–39) ።

ፊልጶስ ጉዞውን በመቀጠል በባሕር አጠገብ ወደምትገኘው አዛጦን ወደምትባለው ከተማ ሄደ ። ከዚያችም ከተማ በስተቀር ለፍልስጥኤም ዋና ወደብ ወደነበረችው ቂሣርያ እስኪደርስ ድረስ በባሕር ዳር የነበሩ ከተማዎችን አስተምሯል ።

## ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት

<u>ሐዋርያው ጴጥሮስ (ስምዖን ፣ ኬፋ)</u> ። ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከመከተሉ በፊት በጌንሳሬጥ ባሕር ዓሣ አጥማጅ ነበር። ከተከተለው በኋላ ግን የጰንጠቆስጤ ዕለት የወንጌልን ትምህርት አስተምሮ በአንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ሰዎችን አሳመነ (የሐዋ·2፡41) ። ከእስጢፋኖስ ዕረፍት በኋላ ኢየሩሳሌም ውስጥ ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ሲያስተምርና ታምራት ሲያደርግ ቈይቶ ክርስትና በመላው ፍልስጥ ኤምና በኀረቤት ሀገሮች እንደ ተስፋፋች ስለሰማና ስላየ ልዳ ፣ ኢዮጴ ፣ ቂሣርያ በተባሉ ከተሞች እየዞረ አስተማረ ። ብዙ ታምራትም አደረገ ። ኢዮጴ ሳለ ባየው ራእይ መሠረት የወንጌልን ቃል ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአሕዛብም መስበክ መገባቱን በማመን በቂሣርያ የነበረውን አረማዊ ውን የመቶ አለቃ ቆርነሌዎስን ከነቤተ ሰቡ አጠመቀው (የሐዋ· 10፡48)።

በ36 ዓ·ም ከፋሲካ በዓል ቀደም ብሎ ጴጥሮስ ታሰረ ። ሞቱም ከበዓሉ በኋላ እንዲፈጸም ተወስኖ በእስር ቤት በጥብቅ ሲጠበቅ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ የታሰረበትን ሰንሰለት ፈትቶ እስከ መጨረሻው የእስር ቤቱ የብረት በር ድረስ መርቶ አውጥቶ ከጎዳው ካደረሰው በኋላ ተሰወረው ። እሱም ክርስቲያኖች በአንድነት ወደሚሰበሰቡበት ወደማር ያም ቤት ሄዶ ላገኛቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያደረገለትን ምሕረት ነግሮ ወደ ሌላ ቤት ሄደ ።

በ50 ዓ·ም ጴጥሮስ ኢየሩሳሌም ውስጥ በተደረገችው በሐዋርያት ጉባኤ ተካፋይ በመሆን ለተላለፈው ውሳኔ መሳካት ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል (የሐዋ·15፡7–11) ። ከሐዋርያት ጉባኤ በኋላ ጳውሎስ አንጾኪያ ውስጥ ከጴጥሮስ ጋር እንደተገናኙ ይጽፋል (ገላ 2 ፡ 11) ። ጴጥሮስ በስሙ የሚጠሩ ሁለት መልእክታት ጽፏል ።

የሮም ንጉሠ ነገሥት ኔሮን (37–68 ዓ·ም) በክርስቲያኖች ላይ ባስነሣው ስደት ከብዙ ሰማዕታት ጋር ጴጥሮስ በመስቀል የቁልቁሊት ተሰቅሉ ፤ ጳውሎስ አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ በሰማዕትነት ዐረፉ ።

የጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እንዲህ ይላሉ ፤ በኔሮን የታዘዘው ስደት እንደተጀመረ ክርስቲያኖች ጴጥሮስን ለጊዜው ዘወር ብሎ ከሞት በመትረፍ ወንጌልን የማስተማር ተግባሩን እንዲቀጥል በማሰብ እንዲሸሽ ስለ ለመኑት እሽ ብሎ የከተማዋን ቅጽሮች ወጣ እንዳለ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ሮም ከተማ ሲገባ ተገለጸለት ። ጴጥሮስም "ጌታ ሆይ ወዴት ትሄዳለህ?" ብሎ ቢጠይቀው "እንደገና ለመሰቀል ወደ ሮም እሄዳለሁ" ብሎ መለሰለት ። ይህንንም እንደሰማ ጴጥሮስ ልቡ ጥልቅ በሆነ ስሜት ስለተነካና እሱም ሰማዕትነት እንዲቀበል የጌታ ፈቃድ መሆኑን ስለተገነዘበ ወደ ሮም ተመልሶ "ጌታ እንደተሰቀለው ያለ ስቅለት ስለማይገባኝ ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ" ብሎ በመስቀል በሰማዕትነት ዐረፈ ። ጴጥሮስና ጳውሎስ ያረፉትም በ66 ዓ·ም· ነው ።

በ2ኛው መቶ ዘመን የነበረው ጋይዮስ ጴጥሮስ በቫቲካን ኮረብታ ፣ ጳውሎስ በኦስቲያ መንገድ መቀበራቸውን መስክሯል ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም የዕረፍታቸውን መታሰቢያ በዓል ሐምሌ 5 ቀን ታከብራለች ።

ሉቃስ የጳውሎስ ደቀ መዝሙር ስለነበረ በጻፈው በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የጳውሎስን ሥራ አብራርቶ ሲጽፍ የጴጥሮስን በመጠኑ ጽፏል ። በአራቱ ወንጌላት ውስጥ ግን ከሐዋርያት ሁሉ ስለ ጴጥሮስ የተጻፈው ይበዛል ።

<u>ሐዋርያው ጳውሎስ</u>፡ ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም ውጭ ከሚኖሩ የብንያም ዘር ከሆኑ አይሁድ (ፈሪሳውያን) ጠርሴስ በተባለች ቦታ ተወለደ። ክርስትናን ከመቀበሉ በፊት ሳውል ይባል ነበር ። አባቱ የሮማዊነት ዜግነት ዕድል ያገኘ ሰው ስለነበር ፣ ይህ ዜግነት ለልጁ ለጳውሎስ ተላለፈ። ወላጆቹ የአይሁድን ሃይማኖት የሚያስተምር ረቢ (መምህር) እንዲሆንላቸው ስለፈለጉ ለትምህርት ወደ ኢየሩሳሌም ሰደዱት ። እሱም ከትምህርቱ ጋር የዕለት ምግቡን ለማግኘት የሚያስችለውን ድንኳን አሰፋፍን ተማረ (የሐዋ· 18፡3) ። በኢየሩሳሌም ዝነኛ ለነበረው የሕግ መምህር

ለገማልያል ተማሪ በነበረበት ጊዜ አብረውት ይማሩ ከነበሩት ይልቅ በጣም ብልኅና ንቁ እንደነበረ፤ እንዲሁም አባቶቹ አይሁድ ለአስተማሩት ሃይማኖት ቀናተኛ እንደነበረ ራሱ ይናገራል (ገላ·1፥14) ።

የወንጌል ትምህርት ለጳውሎስ ከኦሪት የሚለይ ትምህርት መስሎ ስለታየው ለኦሪት ሃይማኖት ቀንቶ ክርስቲያኖችን ያሳድድ ጀመር (ገላ·1፥13) ። እነሱንም በሚያሳድድበት ጊዜ እምነተ ጠንካራነታቸውን ፥ ታጋሽነታቸውን ፥ ደፋርነታቸውን ፥ በመካከላቸው የነበረውን ፍቅር ፥ እንዲሁም የእስጢፋኖስን ንግግሮች ስለተመለከተ በልቡ ውስጥ አንድ ዓይነት የአድናቆት ስሜት ተፈጥሮበት ነበር ።

ከፍልስጥኤም ውጭ በሶርያ ውስጥ በምትገኘው በደማስቆ ብዙ አይሁድ ክርስትናን እንደተቀበሉ በሰማ ጊዜ ፥ ወዲያው እነዚህን ክርስትናን የተቀበሉትን አይሁድ አስሮ ወደ ኢየሩሳሌም ለማምጣት የሚያስችለውን ደብዳቤ ከሊቀ ካህናቱ ተቀብሎ ፥ መንገድ መሪዎችን አስከትሎ ፥ ወደ ደማስቆ ሲሄድ ወደ ከተማው በቀረበ ጊዜ በላዩ ላይ ኃይለኛ የመብረቅ ብርሃን ስለ አንጸባረቀበት ወደ መሬት ወደቀ ። ወዲያውም "ሳውል ፥ ሳውል ፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ?" የሚል ድምፅ ሰማ ። እሱም "ጌታ ሆይ ፥ ማን ነህ?" አለው ። ጌታም "አንተ የምታሳድደኝ እኔ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ ፥ በተሳለ ችንካር ላይ ብትቆም ላንተ ይብስብሃል ..." ብሎ መለሰለት (የሐዋ· 9፥4–5፤ 26፥14) ። ከዚያም በኋላ ሐናንያ በጌታ ትእዛዝ በጳውሎስ ላይ እጁን ጫነበት ። አጠመቀውም ። ሦስት ቀን ሙሉ ታውረው የነበሩ ዐይኖቹም ተከፈቱ ። እህልም በልቶ በረታ ። ወዲያውኑ በየምኩራቦቹ እየዞረ አይሁድ በሙሉ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ድኅነትን እንዲያገኙ በማለት ሲሰብክ ፥ ለሃይማኖታቸው ቀናተኛ የሆኑ አይሁድ ሰምተው እንዴት ክርስቲያኖችን ያሳድድ የነበረው ይህ የክርስትናን ሃይማኖት ያስተምራል ? በማለት በጥብቅ ተቃወሙት ። ይህም መቃወም አደገኛ ስለነበረ ፥ አይሁድ እሱን ለመግደል ስለቈረጡ እንዳያመልጣቸው የከተማውን ቅጥር ዙሪያ ሌት ከቀን በጥብቅ ያስጠብቁ ጀመር ። ክርስቲያኖችም ይህንን የወንጀል አድማ ስለሰሙ ጳውሎስን በቅርጫት ውስጥ አድርገው በቅጥሩ ላይ አውርደው እንዲያመልጥ አደረጉ ። እሱም ወደ ዓረብ ሀገር ሄደ ፤ ከዚያም ወደ ደማስቆ ተመልሶ የሐዋርያነቱን ሥራ ሲሠራ ቈይቶ ከ3 ዓመታት በኋላ ከጌታ ደቀ መዛሙርት ጋር ለመተዋወቅ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ።

ሐዋርያት ግን ስለ ጳውሎስ ማመን ተጠራጥረው ሳለ ጳውሎስን በደንብ የሚያውቀው በርናባስ ስለጠንካራ እምነቱ አረጋግጦ ነገራቸው ። ኢየሩሳሌም የነበሩ አይሁድ ሊገድሉት ስለዶለቱበት ከ15 ቀኖች ይበልጥ ሳይቈይ ወደጠርሴስ ሄደ (ገላ· 1 ፥ 18) ።

በአንጾኪያ የክርስቲያኖች ቍጥር እየበዛ ስለሄደ ከኢየሩሳሌም በርናባስ ሄዶ የተቻለውን ያህል ሲያስተምር ቈየ ። ነገር ግን ለዚህ ከባድ ሥራ የጳውሎስም ርዳታ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ጳውሎስን ከጠርሴስ ወደ አንጾኪያ አመጣው ። እዚያም ከፍ ያለ የማስተማር ተግባሩን ጀመረ ። ጳውሎስ በሚያስተምርበት ጊዜ ከአይሁድ ወገን ክርስትናን የተቀበሉ ሰዎች ከአሕዛብ ወገን ክርስቲያን የሆኑትን ሁሉ ከጥምቀት በኋላ እንደ ግዝረት ያሉትንና የፈሪሳውያንን ልማድ በጥብቅ መጠበቅ ይገባችኋል እያሉ ስለ አስቸገሩአቸው ፥ ክርስትናን የተቀበሉ አሕዛብ ያይሁድን ልማድ በመጠበቅ ቀስ በቀስ የክርስትናን እምነት ትተው ወደ አይሁድ እምነት ጭልጥ ብለው እንዳይሄዱና ፥ በዕድሜ የገፉትንም ክርስትናን ከመቀበላችሁ በፊት ተገዘሩ ሲሉአቸው ያመናል እያሉ ወደ ጣዖት አምልኮአቸው እንዳይመለሱ ስለ ፈራ ፥ ከበርናባስ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከላይ የተጠቀሰውን በክርስትና መስፋፋት ላይ የተፈጠረውን አደገኛ እንቅፋት ለጴጥሮስ ፥ ለዮሐንስ ፥ ለያዕቆብና በኢየሩሳሌም ለነበሩት ሁሉ ገልጦ አስረዳቸው ። ሐዋርያትም የጳውሎስን ሐሳብ መርምረው ከተከራከሩበት በኋላ ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን የተቀበሉ ሁሉ ከአይሁድ ወገን ክርስትናን ከተቀበሉት ጋር ትክክል መሆናቸውንና ግዝረትን ፥ ሌላውንም የፈሪሳውያንን ልማድ ለመጠበቅ የማይገደዱ መሆናቸውን በአንድ ቃል አጸደቁ ። የዚህም ጉባኤ ውጤት በጳውሎስ ፥ በበርናባስና ከኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን በተላኩ ሰዎች እጅ በአንጾኪያ ፥ በሶርያ ፥ በኪልቅያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በተላከላቸው ጊዜ ፥ ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን የተቀበሉት ሰዎች ደስታ በጣም ከፍ ያለ ሆነ ። ይህችም በ50 ዓ·ም ኢየሩሳሌም ውስጥ የተደረገችው የሐዋርያት ጉባኤ ተብላ ትጠራለች ። በዚህ አኳኋን ጳውሎስ ክርስትናን ከመዳከምና እስከ መጥፋት ከመድረስ አዳናት ለማለት ይቻላል ። ምክንያቱም በዘመናችን ያሉት ክርስቲያኖች ብዙዎቹ ከአሕዛብ ወገን የነበሩ ናቸው እንጂ ከአይሁድ ወገን ከነበሩት በመጠኑ ናቸው (የሐዋ·15፥2–35) ።

ጳውሎስ በሜዲትራንያን ባሕር ዳር ለዳር በሚገኙ ሀገሮች በኢየሩሳ

ሌም ፣ በሮማ ፣ በአቴና ፣ በቆሮንቶስ ፣ በኤፌሶን ፣ በተሰሎንቄ ፣ ከአንጾኪያ አንስቶ እስከ እስጳኝ ድረስ ባሉ ሀገሮች ክርስትናን ከፍ ባለ ትጋት አስተምሮአል ። ሕዝቡን አስተምሮ ለመሠረታቸውም አብያተ ክርስቲያ ናት የእምነት ማጽኛ ፣ የግብረ ገብነት መሪ የሚሆኑ 14 መልእክታት ጽፎላቸዋል ።

አራት ጊዜ ባደረጋቸው ጉዞዎች በየቦታው እየዞረ በሚያስተምር በት ጊዜ አብረው በመሥራት የረዱት በርናባስ ፣ ወንጌላዊው ማርቆስ ፣ ሲላስ (ስልዋኖስ)፣ ቲቶ ፣ ጢሞቴዎስ ፣ ወንጌላዊው ሉቃስና ሌሎችም ነበሩ ።

<u>ሐዋርያው ዮሐንስ</u> ። ጌታ ይወደው የነበረው የዘብድዮስ ልጅ ዮሐንስ በፍልስጥኤም ፣ ከፍልስጥኤም ውጭም ክርስትና እንድትስፋፋ ከጴጥሮስ ጋር በመተባበር አስተምሯል (የሐዋ· 4 ፣ 1 — 22 ፣ 8 ፣14) ። እንዲሁም ኢየሩሳሌም ውስጥ በተደረገችው በሐዋርያት ጉባኤ ተገኝቶ ለተፈጸሙት ሥራዎች ተካፋይ ሆኖ ነበር (ገላ· 2 ፣ 9) ። ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ እመቤታችንን እንዲያገለግላት አደራ የሰጠው ለዚሁ ለወንጌላ ዊው ዮሐንስ ነበር (ዮሐ· 19 ፣ 26) ።

ከጳውሎስ ዕረፍት በኋላ በ66 ዓ·ም ዮሐንስ ከኢየሩሳሌም ወደ ኤፌሶን ሄዶ እዚያ ተቀምጦ በትንሿ እስያ የነበሩትን አብያተ ክርስቲያ ናት በማስተማር ሲያገለግል ቆየ ። በዶሚቲያኖስ ዘመነ መንግሥት (81—96 ዓ·ም) ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት ተሰዶ በእስር ቤት ሳለ እዚያው ራእየ ዮሐንስን ጻፈ ። ከዶሚቲያኖስ ሞት በኋላ ወደ ኤፌሶን ተመልሶ ፣ "ልጆቼ እርስ በርሳችሁ ተፋቀሩ ። የጌታ ትእዛዝ ይህች ስለሆነች ፣ ይህችን በመፈጸም ትእዛዛቱን ሁሉ ለመፈጸም ትችላላችሁ" እያለ ያስተምራቸው ነበር ። ዮሐንስ ኤፌሶን ውስጥ እስኪያረጅ ድረስ ቆይቶ በትራይአኖስ ዘመነ መንግሥት (98—117 ዓ·ም) መጀመሪያ ላይ ዐረፈ ይባላል ። ጥቂቶች ደግሞ በማቴ· 16፣28 ፣ በዮሐ· 21፣22 የተጻፈውን በመከተል አልሞተም ይላሉ ። እሱም ከራእየ ዮሐንስ በስተቀር በስሙ የሚጠሩ አንድ ወንጌልና ሦስት መልእክታት ጽፏል ። በጻፈው ወንጌል ውስጥ ምሥጢረ ሥላሴን አምልቶና አጉልቶ ስለጻፈ ነባቤ መለኮት (ቴዎጎሎስ) የሚል ስም ተሰጠው ።

<u>ሐዋርያው ያዕቆብ</u> ። የዮሐንስ ወንድም ያዕቆብ ኢየሩሳሌም ውስጥ ለተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ በማስተማር ከፍ ያለ

አገልግሎትን አበርክቷል ። የክርስትናን ትምህርት በትጋት ማስተማሩ በአይሁድ ዘንድ እንደ ወንጀል ስለ ተቈጠረበት ፣ ሄሮድስ አግሪጳ አይሁድን ለማስደሰት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በ44 ዓ·ም አንገቱን በሰይፍ ተቀርጦ በሰማዕትነት ዐረፈ (የሐዋ· 12 ፥ 2) ።

ሐዋርያው እንድርያስ ። የጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ለሐዋርያ ነት በጌታ ቃል መጀመሪያ ተጠራ ። ጌታንም ከመከተሉ በፊት የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር (ዮሐ· 1 ፥ 41) ። መጀመሪያ የስብከት ሥራውን በፍልስጥኤም ጀመረ ። ቀጥሎም በእስኪሲያ ፣ በስራኪ ፣ በመቄዶንያ ፣ በትንሿ እስያ ፣ በግሪክ ሀገር አስተማረ ። የቊስጥንጥንያን ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ እሱ ነው ይላሉ ። ፓትራ በምትባለዋ ሀገር ሲያስተምር በጣዖት አምላኪዎች እጅ በመስቀል ላይ በደንጊያ ተወግሮ በሰማዕትነት ዐረፈ ። የሐዋርያው እንድርያስን አጽም (ራስ ቅል) የኢጣሊያ የመስቀል ጦረኞች በ1208 ዓ·ም ከቊስጥንጥንያ ወደ ሮም ወስደውት ሲኖር በ1964 ዓ·ም ፖፕ ጳውሎስ 6ኛ ለግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተመልሶ እንዲሰጥ አደረገ ።

ሐዋርያው ቶማስ (ዲዲሞስ) ። ጌታ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለሐዋርያት በተገለጠበት ጊዜ ቶማስ ስላልነበረ ፣ የጌታ መከራ መስቀልን ተቀብሎ መሞት እጅግ አሳዝኖት ለብቻው ሆኖ ሲያዝን ከቈየበት ቦታ ሲመለስ ጌታን አየነው ቢሉት ፣ ሳላይ አላምንም አላቸው ። ጌታም እንደ ገና ለሁሉም ተገለጠላቸው ። በዚያን ጊዜ ቶማስ በጣቱ የጌታን የተወጋ ጎኑን ፣ የተቸነከረውን እጁንና እግሩን ዳስሶ አይቶ አመነ (ዮሐ· 20 ፥ 19—28) ። ቶማስ በፋርስ በሕንድ አስተማረ ።

ሐዋርያው ማቴዎስ (ሌዊ) ። ማቴዎስ የቀረጥ ሥራውን በሚያከና ውንበት ጊዜ ጌታ ስለጠራው ወዲያው በቤቱ ታላቅ ግብዣ አድርጎ ጓደኞቹ የነበሩ ቀራጮችን ወደ ጌታ አቅርቦ ካገናኛቸው በኋላ ሁሉንም ትቶ ተከተለው (ሉቃ· 5 ፥ 27—32) ። ጌታን ከመከተሉ በፊት ሌዊ ይባል ነበር (ማር· 2 ፥ 14) ። ከተከተለው በኋላ ግን ማቴዎስ ተብሎ ይጠራ ጀመር (ማቴ· 9 ፥ 9) ። በስሙ የሚጠራውን ወንጌል የጻፈው እሱው ነው ።

ማቴዎስ መጀመሪያ በፍልስጥኤም ፣ ቀጥሎ በኢትዮጵያ ፣ በፋርስ ፣ በመቄዶንያና በሕንድ አስተማረ ።

ሐዋርያው ፊልጶስ ። የቤተ ሳይዳው ፊልጶስ ጌታ ተከተለኝ ባለው

ጊዜ ወዲያው ጥሪውን በመቀበል ጌታን ከመከተሉም በተጨማሪ ናትናኤልንም ወደ ጌታ ያቀረበ እሱ ነው ። (ዮሐ· 1 ፡ 44 47) ። እንዲሁም የአሕዛብን ወገን (ነገድ) የወከሉ ግሪኮችም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጌታ ቀርበው የተማሩ በፊልጶስና በእንድርያስ አቅራቢነት ነበር (ዮሐ· 12 ፡ 20 22) ።

ፊልጶስ ሳያይ ለማመን የሚያዳግተው ሰው ስለነበር የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ኢየሱስን "ጌታ ሆይ ፡ አብን አሳየንና ይበቃናል" ብሎ ቢጠይቅ ፡ ጌታም "አንተ ፊልጶስ ፡ ይህን ያህል ዘመን ከናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን ? እኔን ያየ አብን አይቷል ፡ እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ ? እኔ በአብ እንዳለሁ ፡ አብም በኔ እንዳለ አታምንምን ? ..." (ዮሐ· 14 ፡ 8 11) በማለት ለክርስትና እምነት መሠረት የሆነውን የእግዚአብሔር አብንና የእግዚአብሔር ወልድን አንድነት ምሥጢር አስረዳው ።

ፊልጶስ ወንጌልን ትንሹ እስያ ውስጥ በምትገኘው በፍርግያ አስተማረ ።

<u>ሐዋርያው በርተሎሜዎስ</u>። ጌታችንን ከተከተለ በኋላ የወንጌልን ትምህርት በዓረብ ሀገር ፡ በሕንድና በአርመን አስተማረ ።

<u>ሐዋርያው ስምዖን (ናትናኤል) ለሕገ ኦሪት ቀናተኛው ፡ ቀነናዊው ፡ የቃናው ሰው</u> ። ለሐዋርያነት ከመጠራቱ በፊት ለሕገ ኦሪት ቀናተኛ ፈሪሳዊ ስለነበር ቀናተኛ ተባለ ። እሱም ወንጌልን በመስጴጦምያ ፡ በግብጽ፡ በሰሜን አፍሪካ ሰበከ (ማቴ· 10 ፡ 4 ፤ ዮሐ· 21 ፡ 2) ።

<u>ሐዋርያው ያዕቆብ</u> ። የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ከፍልስጥኤም በስተቀር ወንጌልን በፋርስና በግብጽ አስተምሯል የሚሉ አሉ ።

<u>ሐዋርያው ይሁዳ (ልብድዮስ ፡ ታዴዎስ)</u> ። ይሁዳ በፍልስጥኤም ፡ በሶርያ ፡ በአርመን ፡ በመስጴጦምያና በፋርስ አስተማረ ።

<u>ሐዋርያው ማትያስ</u> ። ጌታን ሸጦ በገዛ እጁ ታንቆ በሞተው በአስቆሮቱ ይሁዳ ፈንታ በዕጣ በመመረጥ ከሐዋርያት ተራ ተቈጠረ (የሐዋ· 1 ፡ 15 — 26) ። እሱም ወንጌልን በግብጽ ፡ በቀጳዶቅያና በኑብያ ሰበከ ።

<u>ወንጌላዊው ማርቆስ (ዮሐንስ)</u> ። ኢየሩሳሌም ውስጥ ክርስቲያኖች በቤቷ ለጸሎት ይሰበሰቡ የነበረችው የማርያም ልጅ ነው (የሐዋ· 12 ፡ 12)። በርናባስ አጎቱ ነበር ። ከጳውሎስም ጋር አብሮ አስተምሯል ። በተለይ ግን የጴጥሮስ ተከታይና ተማሪ ስለነበር ልጄ ይለዋል (1ጴጥ.

5 ፡ 13) ። ከጴጥሮስ የሰማውን (የተማረውን) መሠረት በማድረግ በስሙ የሚጠራውን ወንጌል መጻፉን የኢራጶሊስ ጳጳስ ፓፒያስ መስክሮአል ። ማርቆስ ወንጌልን በማስተማር የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን መሥርቶ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

የቬኑስ ነጋዴዎች በዘጠንኛው መቶ ዘመን የቅዱስ ማርቆስን አጽም ወደ ሀገራቸው ወስደው በከተማቸው ውስጥ ባለው በታላቁ የቅዱስ ማርቆስ ካቴድራል በክብር አስቀምጠውት ከቈየ በኋላ በ1968 ዓ·ም· ወደ ግብጽ ተመልሶ አዲስ በተሠራው በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር ተቀምጧል (ዐርኖል) ።

<u>ወንጌላዊው ሉቃስ</u> ። አንጾኪያ ውስጥ የግሪክ ወገን ከሆኑ ጣዖት አምላኪዎች ተወለደ ። በጳውሎስ አስተማሪነት ክርስትናን ተቀብሎ የእሱ ደቀ መዝሙር ሆኖ ሲያስተምር ኖረ (2 ጢሞ. 4፡11) ። ሐኪምም ነበር (ቈላ.4 ፡ 14) ። ሠዓሊም እንደ ነበረና የእመቤታችንን ሥዕል በመጀመሪያ የሣለ እሱ ነው በማለት ብዙዎች ይተርካሉ ።

በስሙ የሚጠራውን ወንጌልና የሐዋርያትን ሥራ የጻፈ እሱ ነው ። ከመምህሩ ከጳውሎስ ዕረፍት በኋላ በአካይያ ወንጌልን አስተማረ ። ወንጌልን ሲሰብክ ሲባስ በተባለ ሀገር ውስጥ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ፡ 1ኛ/ ማርቆስና ሉቃስ ቍጥራቸው ከሐዋርያት ሳይሆን ከሰባ ሁለቱ አርድእት ነው ። እንዲሁም ቍጥራቸው ከሰባ ሁለቱ አርድእት የሆነው በኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረው የጌታ ወንድም የተባለው ያዕቆብና ወንድሙ ይሁዳ በየስማቸው የሚጠሩትን መልእክታት ጽፈዋል ።

2ኛ/ ከዚህ በላይ ታሪካቸውን የተመለከትነው የጌታ ደቀ መዛሙርት እላይ በተጠቀሱት ሀገሮች ወንጌልን በትጋት ሲያስተምሩ አንገታቸውን በሰይፍ በመቈረጥ ፡ በመሰቀል ፡ በእሳት በመቃጠል ፡ በመጋዝ በመሰንጠቅና እነዚህን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ሥቃዮችን በመቀበል በሰማዕትነት ዐረፉ ።

## በሐዋርያት ዘመን ስለ ክርስትና መስፋፋት የረዱ ሴቶች

ሴቶች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር ከነበረበት ዘመን ጀምረው ስለ ክርስትና መስፋፋት ከፍ ያለ አገልግሎትን አበርክተዋል ። ጌታ ሐዋርያትን አስከትሎ ወንጌልን በየቦታው እየዞረ

ሲያስተምር ማርያም መግደላዊት ፣ ዮሐና ፣ ሶስናና ሌሎችም ሴቶች በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር (ሉቃ· 8 ፣ 1 — 3) ። የአልዓዛር እኅቶች ማርታ ምግብ በማዘጋጀት ፣ ማርያም የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ያገለግሉት ነበር (ሉቃ· 10 ፣ 38 — 42) ። ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ ሴቶች ሸኝተውታል (ማር. 15 ፣41) ። ተሰቅሎ ሳለ በታላቅ ኀዘን ተውጠው በመስቀሉ ሥር ነበሩ (ዮሐ· 19 ፣ 25) ። ትንሣኤውንም በመጀመሪያ ያበሠሩ ሴቶች ናቸው (ማር· 16 ፣ 1 — 13) ።

የማርቆስ እናት ማርያም ቤቷን ለኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች መሰብሰቢያና መጸለያ አድርጋ ነበር (የሐዋ· 12 ፣ 12) ። ፌቤን በቆሮንቶስ የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነበረች ። ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች የጻፋትን መልእክት የወሰደችለት እሷ ናት (ሮሜ 16 ፡ 1) ። ብዙ ሴቶች ለድኾች ፣ ለሙት ልጆች ምጽዋት በመስጠት ይረዱ ነበር ። ከነሱም አንዷ ጣቢታ ነበረች (የሐዋ· 9 ፣ 36) ።

በሐዋርያት ዘመን ከአሕዛብና ከአይሁድ ወደ ክርስትና የመጡት በዕድሜ የገፉ ሴቶች ቊጥር እጅግ ብዙ ስለ ነበር ፣ የተጠመቁትን ሴቶች ሜሮን የሚቀቡአቸው ፣ የታመሙትንም ቀንዲል የሚቀቡ ሴቶች ነበሩ ። እነሱም ዕድሜአቸው ከስልሳ ዓመት ያላነሰ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ባልቴቶች ነበሩ (1 ጢሞ. 5 ፣ 9 — 10) ። በዚህ አኳኋን ከላይ የተጠቀሱት ባልቴቶች የሚያገለግሉት ሴቶችን ብቻ ስለ ነበር ፣ እንደ ዲያቆኑ መላ የቤተ ክርስቲያንን አባሎች ስለማያገለግሉ የተሟላ የዲቁና ተግባር አልነበራቸውም ።

## ከሐዋርያት ቀጥለው የተነሡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች

ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት ለክርስቲያኖች መመሪያና አጽናኝ እንዲሆናቸው ሐዲስ ኪዳንን እንደጻፉ ሁሉ ፣ ከሐዋርያት ቀጥለው በአንደኛውና በሁለተኛው መቶ ዘመን ላይ የተነሡት የክርስትናን ትምህርት ከሐዋርያትና ከደቀመዛሙርቶቻቸው የተማሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ክርስቲያኖች በደረሱባቸው ስደቶች ምክንያት ተስፋ እንዳይቈርጡ አጽናንተዋቸዋል ። እንዲሁም በየጊዜው በተነሡት መናፍቃን ትምህርት እንዳይታለሉ ለመምከር ፡ የክርስቲያኖችን ፍላጎት ለማርካት ፣ በእምነታቸው ጸንተው በመኖር የእግዚአብሔርን ልጅነት የሚያሰጡአቸውን መጻሕፍት ጽፈዋል ። ጽሑፎቻቸውም የተዘጋጁት በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ትምህርቶች ላይ ተመሥርተው

ነበር ።

ከነሱም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

1ኛ <u>የሮም ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ቀሌምንጦስ (91 — 100)</u> ።

ቀሌምንጦስ ሮም ተወልዶ መንፈሳዊ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ ማዕርገ ክህነትን ከሐዋርያው ጴጥሮስ ተቀብሎ አራተኛው የሮም ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ሆነ ።

እሱም በሮምና በአካባቢዋ ሀገሮች ወንጌልን በትጋት አስተምሮ ብዙዎችን ወደ ክርስቶስ መለሰ ።

አውሳብዮስና አንዳንድ ሊቃውንት ቀሌምንጦስ ክርስትናን የተቀበለ በጳውሎስ አስተማሪነት ስለነበረ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ 4 ፡ 3 ያነሣው በማስተማር ሥራው ረዳቱ የነበረውን ይህንኑ ቀሌምንጦስን ነው ይላሉ ።

ቀደም ሲል ቆሮንቶስ በነበሩ ምእመናን መካከል የተነሣውን ሁከት (1ቆሮ. 1፡10 17) ሐዋርያው ጳውሎስ በምክርና በተግሣጽ ቢያበርደውም ቅሉ ፡ በቀሌምንጦስ ጊዜ ደግሞ ሁከቱ እንደገና ያገረሸው ጥቂት ሰዎች በቅናት መንፈስ በመመራት በካህናቱ ላይ በመነሣታቸው ነበር ። ቀሌምንጦስ ይህንን አሳዛኝ ዜና እንደሰማ እንደዚህ ያለውን መጥፎ ተግባር እንዲተውና በመካከላቸውም ሰላም እንዲሰፍን ለመምከር በ96 ዓ·ም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ጥቅሶች (ትምህርት) ላይ የተመሠረቱ (የተደገፉ) ሁለት መልእክታት ጽፎ በየጊዜው በጸሎተ ቅዳሴ ወቅት ለምእመናን እንዲነበብላቸው በማለት ወደ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላከ ። የቆሮንቶስ ጳጳስ አቡነ ዲዮናስዮስ በ170 ዓ·ም ለሮሙ ፖፕ ለሶቴር በላከው ደብዳቤ በቀሌምንጦስ የተጻፈችው መጀመሪያዪቱ መልእክት በሰንበትና በበዓላት ቀን በቤተ ክርስቲያን ለሚሰበሰቡ ምእመናን በየጊዜው በመነበብ ላይ መሆኗን ገልጾለታል ። እንዲሁም ሄሬኔዎስና ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ ከዚችው መልእክት ጥቅሶችን በጽሑፎቻቸው ውስጥ በማስገባት በሮሙ ጳጳስ በቀሌምንጦስ መጻፏን መስክረዋል ።

ቀሌምንጦስ በዚችው በመጀመሪያዋ መልእክት ውስጥ ስለ ጴጥሮስ ሮም መቀመጥና ማስተማር ፡ ጳውሎስ ወደ እስጳኝ ስላደረገው ጉዞ ፡ ኔሮን ባስነሣው ስደት ጳውሎስና ጴጥሮስ ከብዙ ክርስቲያኖች ጋር በሰማዕትነት ስለማረፋቸው ፡ ማዕርገ ክህነት ከጌታና ከሐዋርያት ሲወርድ ሲዋረድ

ስለመምጣቱና ምእመናንም ሥልጣን ክህነት ያላቸው ካህናት የሚሰጡአቸውን ትምህርት እንዲቀበሉና እንዲታዘዙ መዘተ በማለት ጽፏል ።

የሁለተኛዋ መልእክት (መጽሐፍ) ይዘቷ ምእመናን ንስሐ ገብተው እግዚአብሔርን በሙሉ ልቦናቸው እንዲያገለግሉ ፡ የተቀደሰ ኑሮን እንዲኖሩና ትንሣኤ ሙታን መኖሩን አምነው እንዲቀበሉ የሚገልጽ ስብከት ነው ።

ቀሌምንጦስ ከጳውሎስ መልእክታት ውስጥ ከአንደኛ ቆሮንቶስ ፡ ከሮሜና ከኤፌሶን መልእክታት አንዳንድ (ጥቂት) ጥቅሶችን በጽሑፎቹ ውስጥ አስገብቷል ።

ከላይ የተጠቀሱት የሁለቱ መልእክታት ይዘት ጠቃሚ ከመሆኑ የተነሣ አንዳንድ ሊቃውንት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በማስተካከል ሲቀበሉአቸው ፡ ሌሎች ደግሞ ከአዋልድ (ከአፖክሪፋ) መጻሕፍት ጋር ይቈጥሩአቸዋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም የቀሌምንጦስን መልእክታት ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር በማስተካከል ተቀብላቸዋለች ።

እላይ ከተጠቀሱት በስተቀር በጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ጽሑፎቻቸው ተቀባይነትን እንዲያገኙ በማሰብ በአዘጋጆች ስም ሳይሆን በቀሌምንጦስ ስም የተጻፉ የክሕደት ትምህርቶችን የያዙ ፡ ፕሴውዶ ክሌምንትስ (በቀሌምንጦስ ስም በሐሰት የተጻፉ መጻሕፍት) በሚል ስም የሚጠሩ ብዙ አዋልድ መጻሕፍት በምእመናን ዘንድ ተሰራጭተው ነበር።

ቀሌምንጦስ ከአሕዛብ ብዙዎችን ወደ ክርስትና መመለሱ እንደወንጀል ስለተቈጠረበት በንጉሥ ትራያኖስ (ትራጅአን) ትእዛዝ በስደት ሲንገላታ ከቈየ በኋላ አንገቱ ላይ በመልሕቅ ታስሮ ጥቁር ባሕር ውስጥ ተጥሎ በሰማዕትነት ዐረፈ ።

2ኛ <u>የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ አግናጥዮስ (ቴዎፎሮስ) 35-110 ።</u>

ከቅዱስ ጴጥሮስና ከኤውዲዮስ ቀጥሎ ሦስተኛው የአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ የተሾመው የወንጌላዊው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር አግናጥዮስ ነበር ። ደቀ መዛሙርቱ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ቀርበው "በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን ? " ባሉት ጊዜ ስለ ትሕትና ለማስተማር "ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቁሞ እውነት እውነት እላችኋለሁ … እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ በመንግሥተ

ሰማያት የሚበልጥ እሱ ነው" (ማቴ·18፡ 1–4) በማለት በመካከላቸው ያቆመው ሕፃን አግናጥዮስ ነበር ። ስለዚህ አንዳንድ ሊቃውንት ለአግናጥዮስ በግሪክኛ (በጽርዕ) የተሰጠው ቴዎፎሮስ የሚለው ስም እግዚአብሔር ወልድ በእቅፉ የተሸከመው ማለት ነው ሲሉ ፣ ሌሎች ደግሞ ራሱ አግናጥዮስ እግዚአብሔርን በመላ ልቡ (ሰውነቱ) የተሸከመ ማለት ነው ይላሉ ።

አግናጥዮስ ሰማዕትነትን ለመቀበል በእስር በሮማውያን ወታደሮች ታጅቦ ከሶርያ ወደ ሮም ሲወሰድ እዝሚርን በሰነበተበት ጊዜና ሮም እስኪደርስ ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ በዚያ በስደቱና በመከራው ዘመን ክርስቲያኖች ለካህናት እንዲታዘዙ ለመምከር ፣ ለማጽናናት ፣ ከመናፍቃን ትምህርት እንዲርቁ በማለት በሮምና በትንሿ እስያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አጫጭር ለክርስቲያኖች በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሰባት መልእክታት ጽፏል ። ይኸውም ወደ ሮም ሲጓዝ እዝሚርን ውስጥ የአቡነ ፖሊካርፕ እንግዳ ሆኖ በሰነበተበት ወቅት ኤፌሶን፣ ማግኔሲያ ፣ ትራሌስና ሮም ለነበሩት ክርስቲያኖች አራት መልእክታት ጽፎ ሲልክ ፡ ከእዝሚርን ተነሥቶ ጉዞውን በመቀጠል ጥሮአስ እንደደረሰ ፊላደልፊያ ፣ እዝሚርን ለነበሩ ክርስቲያኖችና ለአቡነ ፖሊካርፕ ሦስት መልእክታት ጽፎ ልኳል ። በእስረኛነት ይዘውት የሄዱት ወታደሮችም መልእክታቱን በሚጽፍበትና በሚልክበት ወቅት አንዳችም መሰናክል (ተቃውሞ) አላደረጉበትም ።

አንዳንድ ሊቃውንት ቀደም ሲል ምንም ያልጻፈው አግናጥዮስ እዝሚርን ሲደርስ በዛ ያሉ መልእክታትን መጻፍ የጀመረው በአቡነ ፖሊካርፕ አነሳሽነት (ጉትጐታ) ምክንያት ጭምር ነበር ይላሉ ። መልእክታቱንም በእጅ በመጻፍ የረዳው የኤፌሶኑ ዲያቆን ብሩሑስ ነበር።

ወደ ሮም በጻፋት መልእክቱ ሰማዕትነት ለመቀበል ስላደረበት ጉጉት ሲገልጽ ፡ በሌሎች መልእክቶቹ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ስለመወለዱ ፣ ወንጌልን ስለማስተማሩ ፡ ስለመሰቀሉ ፡ ስለሞቱና ስለ ትንሣኤው አብራርቶ ጽፏል። እንዲሁም ስለቅዱስ ቊርባንና እውነተኛዋን የክርስትና እምነት ጠባቂዎች ጳጳሳት ስለመሆናቸው ገልጿል ። በተጨማሪም የክርስቶስን ሥጋ መልበስና (መዋሐድና) መከራ መቀበል ከሚክዱ ዶሴቲክስ

ከተባሉት መናፍቃን ትምህርት ክርስቲያኖች እንዲርቁ በመምከር ጽፏል። እንዲሁም ክርስትናን ከመቀበላችሁ በፊት የአይሁድን ሃይማኖትና የረበናትን ልማድ ተከተሉ እያሉ ምእመናንን ግራ ያጋቡ ከነበሩት ቢጽ ሐሳውያን እንዲጠነቀቁና እንዲርቁ ምክሩን ለግሷል ።

መምህሩ ወንጌላዊው ዮሐንስም በወንጌሉና በመልክታቱ ውስጥ እላይ የተጠቀሱት የሁለቱ ኑፋቄዎች አራማጅ የሆኑ አባላት ያስተማሩትን የክሕደት ትምህርት በጥብቅ ተቃውሞ ጽፏል ።

አግናጥዮስ ስለ ሦስቱ ማዕርገ ክህነት አብራርቶ ጽፏል ። አግናጥዮስ በክርስትና እምነቱ በመጽናቱና ምእመናንም እንዲጸኑ በማስተማሩ በትራይአኖስ ዘመነ መንግሥት በክርስቲያኖች ላይ በተነሣው ስደት ወቅት በ110 ዓ·ም ወደ ሮም ተወስዶ ኮሎሴየም በተባለው የቲያትር ቦታ ትርእይቱን በፈንጠዝያ በሚመለከተው በሮማ ሕዝብ ፊት ለአንበሶች በመጣል በሰማዕትነት ዐረፈ ። ከአውሬዎች የተረፉት አጽሞቹ አብረውት ወደሮም በሄዱት ወዳጆቹ ወደ አንጾኪያ ተወስደው በክብር ተቀምጠዋል ይባላል ።

3ኛ/ <u>የእዝሚርን ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ፖሊካርፕ (አቡሊካርዮስ) 69-155 ።</u>

ፖሊካርፕ እዝሚርን ውስጥ በ69 ዓ·ም ተወለደ ። እሱም ሐዋርያት ወንጌልን በዓለም አስተምረው ካለፉ በኋላ ኤፌሶን ውስጥ በሕይወት የነበረው የወንጌላዊው ዮሐንስ ደቀመዝሙርና የኢሬኔዎስ አስተማሪ ነበር ። በመምህሩ በዮሐንስ የእዝሚርን ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሹሞ ሳለ ክርስቲያኖችን ለማጽናናትና ከመናፍቃን ትምህርት እንዲርቁ ለመምከር ሲል ብዙ መልእክታት ጽፏል ። ከመልእክታቱም ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ያለችው ወደ ፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን የላካት መልእክት ብቻ ናት ። ይህቺውም መልእክት የተጻፈችበት ምክንያት የሚከተለው ነው ። ቅዱስ አግናጥዮስ ሰማዕትነት ለመቀበል ወደ ሮም ሲጓዝ ተገናኝተው ላነጋገሩት የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ለእምነታቸው ማጽኛ የሚሆን መልእክት ቅዱስ ፖሊካርፕ አዘጋጅቶ እንዲልክላቸው እንዲጠይቁት ነግሮ በመከራቸው መሠረት የአግናጥዮስን መልእክታት ቅጅዎችና የራሱን <u>መልእክት</u> ጭምር እንዲልክላቸው ፖሊካርፕን ጠየቁት ። እሱም የጠየቁትን ክርስቲያኖች ፍላጎት ለማርካት እራሱ ዘንድ የነበሩትንና ዲያቆን ብሩሐስ ያስቀመጣቸውን የአግናጥዮስ መልእክታት ቅጅዎች ሰብስቦ ራሱ ካዘጋ

ጃት መልእክት ጋር ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ላከላቸው ።

ፖሊካርፕ በፊልጵስዩስ መልእክቱ ውስጥ እንደ ወዳጁ እንደ አግናጥዮስ የምእመናን ሞራል የታረመ እንዲሆን ፣ ምእመናን በችግር ላይ ለወደቁት ምጽዋት እንዲሰጡ ፣ ቤተ ክርስቲያን ሀገሪቱን ለሚያስተዳድሩ መጸለይ እንደሚገባት ፣ ስለ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ከኃጢአት ለማዳን ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለድ ወዘተ. አብራርቶ ጽፏል። በዚችው መልእክት ውስጥ ከጳውሎስ መልእክታት፣ ከቀሌምንጦስ ዘሮም መልእክታት ብዙ ጥቅሶችን አስገብቷል ።

የግኖስቲክስን ኑፋቄ መሥራች የሆነውን የቫሌንቲኑስን የክሕደት ትምህርት ተቃውሟል ። እንዲሁም በ155 ዓ.ም ፖሊካርፕ ሮምን ሲጐበኝ የፋሲካን በዓል በራሱና በጓደኞቹ እንደምትመራው እንደ ታናሿ እስያ ቤተ ክርስቲያን አይሁድ በሚያከብሩበት ቀን የሮም ቤተ ክርስቲያንም እንድታከብር ፖፕ አኒሴቱስን ቢጠይቀው አይሆንም ስላለው ሁለቱም ከስምምነት ላይ ሳይደርሱ ወደ ስብከተ ሀገሩ ወደ አዝሚርን ተመለሰ ። በመካከላቸው ግን የመለያየት መንፈስ አልተፈጠረም ነበር ።

ፖሊካርፕ በአንቶንዩ ፒዩ ዘመነ መንግሥት በ155 ዓ.ም ተይዞ ክርስቶስን እንዲክድ ቢጠየቅ 86 ዓመታት ሙሉ ሳገለግለው ያልበደለኝ ንና የሚወደኝን አምላኬን አልክድም በማለት በእምነቱ ስለጸና እዝሚርን በነበረው የጨዋታ እስታዲየም (ቦታ) ውስጥ በተሰበሰበው ሕዝብ ፊት በእሳት ተቃጥሎ በሰማዕትነት ዐረፈ ። ከቃጠሎው የተረፉ አጽሞቹም በክርስቲያኖች ተወስደው ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክብር መቀመጣቸው ይተረካል ።

እላይ ከተጠቀሱት ሌላም እንደ ኢራቅሊስ ጳጳስ እንደ ፓፒያስ የመሳሰሉም ተነሥተው ክርስትናን አስተምረዋል ።

## የስደት ዘመኖች (ዘመነ ሰማዕታት) 64–313 ዓ.ም
## ቤተ ክርስቲያን ስለ ቀጥተኛው እምነቷ የተጋደለችበት ዘመን ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት እንቅፋት የሆኑትና በክርስቲያኖች ላይ የተደረገውን ስደት ያመጡት ምክንያቶች

ክርስትና መስፋፋት እንደ ጀመረች ወዲያው እርምጃዋን የሚያሰናክሉ ከፍ ያሉ እንቅፋቶች ገጠሟት ። ከ64–313 ዓ.ም ድረስ በክርስቲያኖች ላይ ከፍ ያለ ሥቃይና ስደት ደረሰባቸው ። ጌታ በምእመናን ላይ ይህ

እንደሚደርስባቸው ቀደም ብሎ እንዲህ ሲል ተናግሯል ፡ "እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተንን ደግሞ ያሳድዷችኋል" (ዮሐ· 15፡20 ፡ ማቴ·5፡11) ።

በዚያን ጊዜ ከነበሩት ከዓለም ሃይማኖቶች አንዱ ነገሥታቱን ማምለክ ስለነበረ ፡ እነሱን የማያመልክና መሥዋዕት የማያቀርብ እንደ ወንጀለኛ ይቈጠር ነበር ። ስለዚህ የሮም ነገሥታት አማልክት ነንና አምልኩን ሲሉ ፡ ክርስቲያኖች የምናመልክ እግዚአብሔርን ነው ። ነገሥታቱ ግን ገዥዎቻችን ስለ ሆናችሁ ከልብ በመውደድ እናከብራችኋለን ስላሉ እንደ ወንጀለኞች ተቈጠሩ ። ስለዚህ ነገሥታቱንና ጣዖታቱን አለማምለካቸው እንደ በጥባጮችና አደገኞች አስቈጠራቸው ። ሰላማዊነታቸውንም ለማስረዳት ቢሞክሩ ሰሚ አጡ ። ጣዖት ጠራቢዎች ሥራቸው እንዳይቋረጥ በማሰብ ፡ አይሁድም ሕዝባቸው ወደ ክርስትና እምነት ጭልጥ ብሎ እንዳይሄድ በመፍራት ክርስቲያኖችን እንደ ጠላት ይመለከቷቸው ነበር ።

## ከሕዝቡ ዘንድ በክርስቲያኖች ላይ የቀረቡት ስብቀቶችና የሐሰት ክሶች የሚከተሉት ናቸው

1ኛ/ ክርስቲያኖች ጣዖት ማምለክን እምቢ ብለው እውነተኛውን አምላክ በማምለካቸው አምላክ የሌላቸው ከሐዲዎች ተባሉ ።

2ኛ/ የተሰበሰበውን ሕዝብ ለማስደሰት ከግብረገብነት ውጭ ወደሚሠሩባቸው የቲያትር ቦታዎች ፡ ሰዎችና አውሬዎች ፡ እንዲሁም ሰዎችና ሰዎች ወደሚዋጉባቸውና ያለ ወንጀል በግፍ የታሰሩ እስረኞች ለአንበሶች ወደሚጣሉባቸው ቦታዎች ክርስቲያኖች ለማየት ስለማይሄዱ ግማሽ ሰዎች ተባሉ ።

3ኛ/ የጌታን ሥጋና ደም በመቀበላቸው ሕፃናትን እያረዱ ደማቸውን ጠጥተው ሥጋቸውን ይበላሉ ተባሉ ።

4ኛ/ በሮም ግዛት ውስጥ ረኀብ ፡ ቸነፈር ፡ የመሬት መንቀጥቀጥና እነዚህን የመሳሰሉ በደረሱ ቍጥር በከሐዲዎች በክርስቲያኖች ምክንያት የሮም አማልክት ተቈጥተው ያወረዱብን ቅጣቶች ናቸው ብለው ያምኑ ነበር ።

እንደነ ኰአድራቱስ ፡ አሪስቲዲስ ፡ ጁስቲን ፡ ታቲያን ፡ አቴናጎራስ ፡ ቴዎፍሎስ ዘአንጾኪያ ወዘተ· የመሳሰሉ አፖሎጂስቶች ለክርስትና

እምነት ጠበቃ (ተሟጋች) በመሆን ከሕዝቡ ፣ ከገዥዎችና ከነገሥታቱ ፊት ድረስ እየቀረቡ በቃልና በጽሑፍ ከላይ የተጠቀሱት ክሶች ውሸት መሆናቸውን ፤ በዓለም ካሉት እምነቶች ሁሉ እውነተኛዋ ሃይማኖት ከአሪት ጀምሮ ትንቢት በተነገረለት በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተችው ክርስትና ብቻ መሆኗን ፤ የክርስትናም ትምህርት የሕዝቡን ጠባይ የሚያርም መሆኑን በመግለጽ ይከራከሩ ነበር ። በዚህ አኳኋን ክርስቲያኖች የመንግሥትን ሕግ አክባሪዎችና እውነተኞች ሲሆኑ ሳለ ፣ በክርስቲያኖች ላይ የሚያሳብቁት አይሁድና ክርስቲያኖችን የሚያሳድዱ አሕዛብ ሕገ ወጦች መሆናቸውን ያስረዱ ነበር ። እነዚህም ሊቃውንት ይህንን እውነተኛ ነገር መናገራቸውና በጽሑፍ ማስፈራቸው እንደ ወንጀል ተቈጥሮባቸው በሰማዕትነት ዐረፉ ።

## የስደት ዘመኖች በሁለት ይከፈላሉ

1ኛ/ ከ64–250 ዓ·ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላ አጥፏቸው የሚል ዐዋጅ ስላልታወጀ ፣ በአንድ ሀገር የነበሩ ክርስቲያኖች ሲሠቃዩ ፣ በሌላ ሀገር የነበሩት ደግሞ በሰላም ይኖሩ ነበር ።

2ኛ/ ከ250–313 ዓ·ም ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ ምንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ በማቋረጡ ምክንያት ዕረፍት ቢያገኙም ፣ ክርስቲያኖች እንዲጠፉ ጠቅላላ ዐዋጅ ስለታወጀ ያለርኅራኄ በጭካኔ ተፈጁ ።

### በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መቶ ዘመናትና በአራተኛው መጀመሪያ በክርስቲያኖች ላይ ከታወጁት አሰቃቂ ሥቃዮች ከዚህ በታች ዋና ዋናዎችን እንመልከት

1ኛ/ <u>በኔሮን ትእዛዝ የተነሣው ስደት (54–68 ዓ·ም)</u> ።

በ64 ዓ·ም የሮም ከተማ ሁለት ሦስተኛው በታላቅ የእሳት ቃጠሎ አመድ ሆነ ። ብዙ ሰዎችም ተቃጠሉ ። ይህንንም ቃጠሎ ያስነሣው ራሱ ኔሮን ነበር ። ምክንያቱም አሮጌው ከተማ ጠፍቶ አዲስ ከተማና ሰፊ ቤተ መንግሥት እንዲሠራለትና ቃጠሎውንም እያየ ለመደሰት ስለፈለገ ነው። በሀብቱ መቃጠልና በዘመዶቹ ማለቅ ከተቈጣው ሕዝብ ለማምለጥ ኔሮን በሐሰት ይህን ቃጠሎ ያስነሡት ክርስቲያኖች ናቸው ስላለ ፣ ከ64–68 ዓ·ም ድረስ በሮም ከተማ ውስጥ በሚገኙት ክርስቲያኖች ላይ ከፍ ያለና አሰቃቂ ሥቃይ ተፈጸመባቸው ። ጴጥሮስና ጳውሎስም እዚያው በሰማዕት

ነት ዐረፉ ። ግማሾችን በከብት ቆዳ እየጠቀለሉ ለውሾች ጣሉአቸው ። ሌሎችን ደግሞ በየእንጨቱ ላይ እየሰቀሉ አቃጠሉአቸው ። የቀሩትንም በሰም እየነከሩ በጨለማ ጊዜ እንዲያበሩላቸው በአትክልት ቦታዎች አቃጠሉአቸው ። በመጋዝም ሰነጠቁአቸው ። በዚህ አኳኋን በሮም ከተማ የነበሩት ክርስቲያኖች በሰማዕትነት ዐረፉ ። ከላይ የተጠቀሰው ሥቃይ የተፈጸመበት ቦታ የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን የተሠራበት ቫቲካን የተባለው ስፍራ ነው ።

2ኛ/ <u>በዶሚትያኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት(81–96 ዓ·ም) ።</u>

ዶሚትያኖስ በ81 ዓ·ም በሮም ነግሦ ዐሥራ አምስት ዓመት ገዛ ። እሱም እንደ ኔሮን ጨካኝ ስለነበር በ96 ዓ·ም ክርስቲያኖችን ለማሳደድ አምላክ የሌላቸው (አቴይስቶች) ናቸው ፤ የመንግሥትም ጠላቶች ናቸው ብሎ በማስወራት ልክ በኔሮን ጊዜ የተፈጸመው ዓይነት ሥቃይ ሮም በነበሩት ክርስቲያኖች ላይ ብቻ ሳይሆን ከሮም ከተማ ውጭም በነበሩ አንዳንድ አውራጃዎች ውስጥ በሚኖሩት ክርስቲያኖችም ጭምር እንዲፈጸምባቸው አዘዘ (ዐወጀ) ። በዚያን ጊዜ ብዙ ክርስቲያኖች አለቁ ። በሰማዕትነት ካለቁትም መካከል የጳውሎስ ደቀ መዛሙርት ጢሞቴዎስና አናሲሞስ ይገኙባቸዋል ። ወንጌላዊው ዮሐንስም ወደ ፍጥሞ ደሴት ተወስዶ በእስር ቤት (በግዞት) እንዲኖር የተደረገው በዚሁ ወቅት ነው ።

3ኛ/ <u>በትራይአኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (98–117 ዓ·ም) ።</u>

ትራይአኖስ በሮም ግዛት ሥር በነበሩ አውራጃዎች ለሚገኙ እንደራሴዎቹ ሁሉ ክርስቲያኖችን እንዲያሠቃዩ የሚያዝዝ የተለያዩ የማሠቃየት ዘዴዎችን የያዙ ደብዳቤዎችን ላከ ። እንደነዚህ ያሉ ደብዳቤዎች ከደረሱአቸው አንዱ የትራይአኖስ የቅርብ ወዳጅ ፕሊኒኦስ የተባለው ነበር ። በዚያን ጊዜ ለጣዖት አንሰዋም ፤ ጣዖትም አናመልክም ያሉ ክርስቲያኖች ሁሉ በሞት ተቀጡ ። ሰማዕትነት ከተቀበሉትም መካከል ከያዕቆብ ቀጥሎ የኢየሩሳሌም ጳጳስ የነበረው ስምዖን በስቅላት ፤ የአንጾኪያው ጳጳስ አግናጥዮስ ሮም ተወስዶ ለአንበሶች በመጣል በሰማዕትነት ዐርፈዋል ።

4ኛ/ <u>በማርቆስ አውሬሊያኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (161–180 ዓ·ም) ።</u>

ማርቆስ አውሬሊያኖስ ቸር ሰው ቢሆንም ቅሉ ፣ በክርስቲያኖች ላይ ከባድ ስደት እንዲፈጸምባቸው አዘዘ ።

ሜሌቶንና አቲናጐራስ የተባሉት አፖሎጂስቶች (የክርስትና ጠበቆች ፣ ተሟጋቾች) ለመንግሥት ታማኝና ታዛዥ በሆኑ ክርስቲያኖች ላይ ለምን ጣዖት አላመለካችሁም በማለት በግፍ የታዘዘው የስደት ዐዋጅ በተግባር ላይ እንዳይውል በ170 ዓ·ም በመላ ክርስቲያኖች ስም ያቀረቡትን አቤቱታ ንጉሡ ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት አልተቀበለውም ። ክርስቲያኖች እምነታቸውን እንዲክዱ ቢጠየቁ እምቢ ስላሉ ፣ በዚያን ወቅት (ሰሞን) በግዛቱ የተከሰተው ረሀብ ፣ ቸነፈር ወዘተ· በክርስቲያኖች አምላክ ቢስነት ጣዖቶቻችን ተቈጥተው ያወረዱብን መከራዎች ናቸው በሚል ሰበብ ሰውነታቸው ተበጣጥሶ እስኪወድቅ ድረስ በግርፋትና በተለያዩ ቅጣቶች እየተቀጡ አለቁ ። በዚያን ጊዜ በግፍ ካለቁት ሰማዕታት መካከል ፓራስኬቪ ትገኛለች ። እሷም ስለ ክርስትና እምነቷ ልዩ ልዩ ሥቃይ ከተቀበለች በኋላ አንገቷን በሰይፍ በመቈረጥ በሰማዕትነት ዐረፈች ። እንዲሁም በደቡብ ፈረንሳይ የሊዮን ጳጳስ አቡነ ፎቲኑስ በሰማዕትነት ያረፈው በዚሁ ወቅት ነው ።

5ኛ/ <u>በሴፕቲሚዮስ ሴቪሩስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (193–211 ዓ·ም)</u>።

6ኛ/ <u>በዳክዮስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (249–251 ዓ·ም)</u> ።

7ኛ/ <u>በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ የተነሣው ስደት (284–305 ዓ·ም)</u> ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ከ5–7 ተራ ቍጥር ስማቸው የተጠቀሰው ሮማውያን ነገሥታት በክርስቲያኖች ላይ ያወጁት ስደት ታሪክ በክፍል ሁለት ውስጥ ስለተጻፈ ከዚያ ተመልከት ።

## ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መናፍቃንን በመቃወም ያደረገችው የመንፈስ ተጋድሎ

ቤተ ክርስቲያን እላይ ከተጠቀሱት ከሮማውያን ነገሥታት የደረሱባትን ሥቃዮች በመቀበልና እንዳትጠፋ በመጋደል ላይ ሳለች ፣ ከውስጧ ደግሞ አደገኞች የሆኑ ጠላቶች ተነሡባት ። እነሱም ከሐዋርያት ጊዜ ጀምረው የነበሩት መናፍቃን ናቸው ። መናፍቃን ማለት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ቀጥተኛ እምነት ተቀብለው በማመንና በማስተማር ፈንታ ተቃዋሚ የሆኑ የክሕደት ትምህርቶችን የሚያስተምሩ ናቸው ።

ምንም እንኳ በየጊዜው የተነሡት ልዩ ልዩ መናፍቃን ቍጥር ብዙ ቢሆንም ከዚህ በታች ጥቂቶችን እንመልከት ።

1ኛ የመጀመሪያዎች መናፍቃን ቢጽ ሐሳውያን (ዩዛይዞንዶስ) ይባላሉ ። እነሱም ከአይሁድ ወገን ክርስትናን በመቀበል ተጠምቀው ፡ ተመልሰው ወደ አይሁድ ሃይማኖት ያዘነበሉት ናቸው ። ከአሕዛብ ወገን ክርስትናን የተቀበሉትን አስቀድማችሁ የአይሁድን ሃይማኖትና የረበናትን ልማድ ያዙ እያሉ ያስገድዷቸው ነበር ። ጳውሎስንም በማስተማር ሥራው በጣም አውከውት ነበር ። ነገር ግን በ50 ዓ·ም ኢየሩሳሌም ውስጥ በተደረገችው በሐዋርያት ጉባኤ ተፈረደባቸው ።

2ኛ/ ግኖስቲክ የተባሉት የተለያዩ የኑፋቄ ትምህርቶችን የሚያስተምሩ አንጃዎች ያሏቸው ከሐዲዎች ናቸው ። እነሱም ጥልቅ የሆነ ምሥጢራዊ ዕውቀት ያለን የክርስትና ፈላስፎች ነን በማለት ደግና ክፉ የሆኑ ሁለት ትልልቅ አማልክት አሉ ። ደግ ነገር ሁሉ ከደጉ አምላክ ሲመጣ ፡ ክፉው ነገር ደግሞ ከክፉው አምላክ ይመጣል ። ከነዚህም ከትልልቆቹ አማልክት ሌሎች ትንንሾች ደጎችና ክፉዎች አማልክት ተገኙ ። እነሱም ዘመናት ተብለው ይጠራሉ ። ከደጋጉ አንዱ ኢየሱስ ነው አሉ ። ዓለምን የፈጠረ ከክፉዎች አማልክት አንዱ ነው አሉ ። እንዲሁም ጌታ በምትሀት እንጂ በእርግጥ ሥጋን መዋሐዱን ካዱ ። በሚሰቀልበትም ጊዜ በምትሀት ተለውጦ የስምዖን ቀሬናዊውን ቅርፅ ስለወሰደ ፡ ባለማወቅ ጌታችን ኢየሱስ መስሏቸው አይሁድ የሰቀሉት የጌታን መስቀል ተሸክሞ የነበረውን ስምዖን የተባለውን ቀሬናዊውን ሰው ነው አሉ ። እንዲሁም ግማሾቹ ደግሞ ጌታ በተሰቀለ ጊዜ ሰውነቱን በመስቀል ላይ ትቶ ወደ ሌላ አምላክነት ተለወጠ እያሉና እነዚህን የመሳሰሉ የክሕደት ትምህርቶችን አስተማሩ ። በዚህ አኳኋን በብሉይ ኪዳን ትምህርት መሠረት የዓለምን ፈጣሪ እግዚአብሔርን በመካዳቸው ፡ የወልድንም ሥጋን መዋሐድ ፡ መከራ መቀበሉን ፡ መሞትና መነሣት በመካዳቸው ፡ ከሰው ልጆች መካከልም ድኅነት የሚያገኙ ፍጹም የሆነ መንፈሳዊ ዕውቀት ያላቸው ጥቂቶች ብቻ ናቸው በማለታቸው ቤተ ክርስቲያን ለምታደርገው መንፈሳዊ ተልእኮ አደገኞች ነበሩ ። በተጨማሪም ክርስቲያኖችን ለማታለል በሐዋርያት ስም የክሕደት ትምህርት የያዙ ወንጌሎችንና መልእክቶችን እየጻፉ ለሕዝብ ስላደሉ ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን መጻሕፍት ከእነዚህ መጻሕፍት ለመለየት ቅዱሳት መጻሕፍት አለቻቸው ።

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሐዋርያትና በአርድእት የተጻፉ በልዩ

ልዩ ጊዜና ሀገር ነው ። የተጻፉትም በጠቅላላው ለቤተ ክርስቲያን ነው ። ስለዚህ በሐዋርያት ዘመን እንደዛሬው ተሰብስበው በአንድ ላይ አልተጠረዙም ነበር ። ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስነው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከ2ኛው መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምራ እስከ 5ኛው መቶ ዘመን ድረስ መርምራ ከከሐዲዎች መጻሕፍት ለይታ 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብቻ ተቀበለች ። በዲዮቅልጥያኖስ ትእዛዝ ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት በመውደማቸው ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት ችግር ደርሶባት ስለነበር በዚያን ጊዜ በትልቁ ቈስጠንጢኖስ ትእዛዝ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ለቍስጥንጥንያ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ 50 መጽሐፍ ቅዱስ አስጽፎ አዘጋጀ ።እንዲሁም ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆኑ እንደ ጸሎተ ሃይማኖትና እንደ ምሥጢረ ሥላሴ ያሉ ትምህርቶችን አሰናድታ ለክርስቲያኖች ሰጠች ። የሰማርያው ጠንቋዩ ሲሞን ፣ ሳቶርኔሉስ ፣ ማርሲዮን ፣ ቫሲሊዲስ ፣ ቫሌንቲኑስ ወዘተ ቍጥራቸው ከነዚህ ከሐዲዎች ነው ።

3ኛ/ ሌሎች ከሐዲዎች ደግሞ አንዲትሪአዲክ ይባላሉ ። እነሱም የክርስትና እምነት መሠረት የሆነውን የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የተቃወሙ ናቸው ።

ከነሱም ጳውሎስ ሳምሳጢስ የተባለው የአንጾኪያው ኤጲስ ቆጶስ (260–272 ዓ·ም) "አምላክ አብ ብቻ ነው ። ወልድ ግን በእግዚአብሔር ጥበብ የተሞላ ነው እንጂ አምላክ አይደለም" ብሎ የክሕደት ትምህርት ስለአስተማረ ቤተ ክርስቲያን አውግዛ ለየችው ።

በ3ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተነሣው ሰባልዮስ የተባለው መናፍቅ ደግሞ ሥላሴ አንድ ገጽ አንድ አካል ናቸው በማለት "አንድ የሆነው እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን አብ ፣ በሐዲስ ኪዳን ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ በመሆን በሦስት ዓይነት መንገዶች ተገለጸ " ብሎ የክሕደት ትምህርት አስተማረ ። የእስክንድርያው ዲዮናስዩስ ሰባልዮስን በመቃወም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት አስፋፍቶ ጻፈ ።

## የጥንት ክርስቲያኖች ሥርዓተ እምነት አፈጻጸም

1ኛ/ የጸሎት ቦታዎች ።

ሐዋርያት ለስብከት ወደመላው ዓለም ከመበተናቸው በፊት በጊዜው በነበሩ በምሕራብ አሪቱና ጽርሐ ጽዮን በተባለው በማርቆስ እናት

በማርያም ቤት እየተሰበሰቡ ይጸልዩ ነበር ። ኋላ ግን የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን በፊልጵስዩስ አገር ስለተሠራች ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የጸሎት ቤት መለየት ፣ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ተጀመረ ።

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ምእመናን ባልበዙበት ቦታ ስደትና መከራ በበዛበት ዘመን በየዋሻው ፣ በየቦታው ሥርዓተ እምነታቸውን ይፈጽሙ ነበር ። በ2ኛው መቶ ዘመን ላይም ቤተ ክርስቲያን መሥራትን እያስፋፉ ሄዱ ።

ከዚህም በኋላ ከሠዓሊዎች ፣ ከቅርፅ ዐዋቂዎች ፣ ከወርቅ ሠራተኞች ወገን ምእመናን እየበዙ ስለሄዱ የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራት የሚገልጹ ልዩ ልዩ ሥዕሎች ተሣሉ ። የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ፃሕል፡ ጽዋዕ ፣ ጽንሐሕ ፣ መስቀል ፣ እነሱንም የመሰሉት ሁሉ ተሠሩ ።

2ኛ/ <u>ክርስቲያኖች ይፈጽሟቸው የነበሩ ሥርዓታት ።</u>

ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ካህናት በሚፈጽሟቸው በሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን (ንስሐ ፣ ጥምቀት ፣ ሜሮን ፣ ቍርባን ፣ ክህነት ፣ ተክሊልና ቀንዲል) ለክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ጸጋ ይሰጣቸው ነበር ። ክርስቲያኖች ካመኑ ከተጠመቁ በኋላ በየቀኑ በተለይም እሑድ እየተሰበሰቡ መጀመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንብበው ካህኑ ስብከት ካደረገ በኋላ ንኡሰ ክርስቲያን (ካቴኩሜኒ) የተባሉት ይወጡ ነበር ። ከውስጥ ያሉት ከጸለዩና ከዘመሩ በኋላ ጥዋት ሥጋ ወደሙን ይቀበሉ ነበር ። እንዲሁም ዘወትር ፍቅርን በተመላ መንፈስ ድኻ ሀብታም ሳይባባሉ በአንድ ላይ ይመገቡ ነበር ።

<u>ማስታወሻ</u> ፡ ሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን የተባሉትን ፡ ሌሎች ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይሏቸዋል ።

3ኛ የበዓላት ቀኖች ።

ከጌታ ትንሣኤ በኋላ በሐዋርያት ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣበት ዕለተ እሑድ ሰንበተ ክርስቲያን ተብላ ትከበር ጀመር (ራእይ 1፡10 ፡ የሐዋ·20፡7 ፡ 1 ቆሮ·16፡2) ። አይሁድ ከፈርዖን እጅ ነጻ ሆነው ከግብጽ የወጡበት ፋሲካ የጌታን ሞትና ትንሣኤ በማሰብ ወደ ክርስቲያን በዓልነት ተለወጠ (1ቆሮ·5፡7) ። እንዲሁም አይሁድ ለካህናት ዐሥራት ያወጡበት የነበረው የጰንጠቆስጤ በዓል ለሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ምክንያት በማድረግ ወደ ክርስቲያን በዓልነት ተለ

ወጠ። ረቡዕ አይሁድ ጌታን ለመያዝ የተማከሩበት ፣ ዐርብ ጌታን የሰቀሉበት ቀኖች ስለሆኑ ፡ የጾም ቀኖች አደረጉአቸው ። የሰማዕታትም የበዓላት ቀኖች በየጊዜው ተወስነው ይከበሩ ጀመር ።

ፋኛ/ የክርስቲያኖች ጠባይና ልማድ ።

በመጀመሪያዎቹ በሦስቱ መቶ ዘመናት የነበሩት ክርስቲያኖች ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ያልታየ እጅግ መልካም ጠባይ ነበራቸው ። አይሁድና አሕዛብ ራስን በመውደድና በትዕቢት ተመልተው በነበሩበት ዘመን ክርስቲያኖች ራስ መውደድን አምዘግዝገው ጥለው ከልብ እርስ በርሳቸው ይፋቀሩ ነበር ። ፍቅራቸውንም ድኆችን በመርዳት ፣ የተማረኩትን በገንዘባቸው ነጻ በማውጣት ፣ በሽተኞችን በማስታመም ፣ እንግዶችን በመቀበልና እነዚህን በመሳሰሉ ደጋግ ሥራዎች በመግለጻቸው አሕዛብ "ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚዋደዱ ተመልከቱ" ሲባባሉ ይሰሙ ነበር። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኖች አሽከሮቻቸውን እንደ ወንድሞቻቸው ይመለከቱአቸው ነበር (ኤፌ· 4፡22–32 ፤ 6፡5–9፤ ቈላ·4፡1) ።

የክርስቶስን ፈለግ በመከተል ብዙዎቹ ድንግልናን ፣ ተባሕትዎን ያዙ ። ኋላ ግን በድንግልና ላይ ለአክሊለ ሦክ መታሰቢያ ምልክት ቆብ ያደርጉ ጀመር ። ከቀኑም በ7ቱ ጊዜያት ይጸልዩ ነበር (መዝ·119፡164) ። ሥራቸውንም ሲጀምሩና ሲጨርሱ ፊታቸውን በትዕምርተ መስቀል ያማትቡ ነበር ። ይህ ሁሉ ሲሆን ከስንዴ መካከል አንዳንድ እንክርዳድ እንደማይጠፋ ሁሉ እንዲሁም በዚያን ዘመን እንደ አናንያና ሰጲራ ያሉ ከፉዎች አልጠፉም ነበር (የሐዋ. 5፡1–11 ፤ 6፡1) ። ነገር ግን እንደነዚህ ያሉት ሁሉ የሚገባ ቅጣታቸውን ተቀብለዋል ። በክሕደት ምክንያት የተሳሳቱትም ንስሐ ገብተን እንመለስም ሲሉ ከቤተ ክርስቲያን አባልነት አውግዘው ይለዩአቸው ነበር ።

## በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መቶ ዘመናት የቤተ ክርስቲያን አመራር

ጌታ ለሐዋርያት የዓለምን ሕዝብ እንዲያስተምሩ በሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት (ማቴ·28፡ 19–20) በየሀገሩ እየዞሩ በማስተማር ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ከመሠረቱ በኋላ ፣ ወንጌል ያልተሰበከለትን ሌላውን ክፍለ ሀገር ለማስተማር ሲሄዱ የመሠረቷቸውን አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉና የሚያስተዳድሩ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾሙ ነበር ። የተሾሙትም ለክርስቲያኖች ኃላፊዎች ፣ ጠባቂዎችና የሚፈጸሙ

ትንም አገልግሎቶች የመፈጸም የበላይነት ሥልጣን ነበራቸው ። ኤጲስ ቆጶሳቱም የአገልግሎቱ ሥራ ስለበዛባቸው ቀሳውስትን ሾሙ ። እንዲሁም ለኤጲስ ቆጶሳቱና ለቀሳውስቱ ረዳት እንዲሆኑ ዲያቆናት ተሾሙ ። በዚህ እኳኋን ሦስቱ ማዕርገ ክህነት ለካህናት ተሰጠ ። ከጌታ ለሐዋርያት፣ ከሐዋርያትም ለኤጲስ ቆጶሳት ሥልጣነ ክህነትን የመስጠት ሀብት (ሥልጣን) ተሰጣቸው (ዮሐ·20፡22 23 ፤ የሐዋ· 6፡3–9 ፤ 1ጢሞ·4፡14 ፤ 2ጢሞ· 1፡6፡ ቲቶ 1፡5) ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት ካስተማሩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 5ኛው መቶ ዘመን ድረስ ክርስትና የተሰበከችባቸው ሀገሮች የሚከተሉት ናቸው ።

ፍልስጥኤም ፡ ትንሿ እስያ ፡ አንጾኪያ ፡ ሶርያ ፤ ቆጵሮስ ፤ ቀርጤስ ፤ አቴና ፡ የግሪክ አውራጃዎች ቆሮንቶስ ፡ ኤፌሶን ፤ ተሰሎንቄ ፤ ፊልጵስዩስ፡ ሮም ፡ የዓረብ ሀገር ፡ እስጳኝ ፡ ግብጽ ፤ ኢትዮጵያ ፤ ሰሜን አፍሪካ (ካርቴጅ) ፡ አርመን ፡ ፋርስ ፡ ሕንድ ፡ ፈረንሳይ ፤ ብሪታንያ ፤ ሩማንያና ሌሎችም በሜዲትራንያን ባሕር ዙሪያ የሚገኙ ሀገሮች ናቸው።

## ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት የረዱ የሚከተሉት ናቸው

ሀ) ብሉይ ኪዳን እስክንድርያ ውስጥ ከክርስቶስ ልደት በፊት በዳግማዊ በጥሊሞስ (ፕቶሎሚ) ትእዛዝ (285—246 ዓመተ ዓለም) ከእብራይስጥ ሕዝቡ ወደሚሰማው ወደ ግሪክ ቋንቋ በሰባ ሊቃናት (ረበናት) ስለተተረጐመ ከአሕዛብ ብዙዎቹ በእግዚአብሔር አመኑ ። ቀጥሎም ነቢያት አስቀድመው ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ትንቢት የተናገሩለት ኢየሱስ ሲወለድ በእሱ በማመን ክርስትናን ተቀበሉ ።

ለ) የሮም መንግሥት ዓለምን መግዛቱ ለክርስትና ትምህርት መስፋፋት ጠቀመ ። ምክንያቱም ሰፊው የሮም ግዛት እንደዛሬው በየመንግሥታቱ ስላልተከፋፈለና በየቦታው ቁም ፣ የይለፍ ወረቀት አሳይ የሚል ጠረፍ ጠባቂ ስላልነበረ ፣ አምረው የተሠሩ መንገዶችና የባሕር ወደቦች ስለነበሩና እንዲሁም በወታደሮች ትጋት ቀማኞች ስለጠፉ ሰባኪዎች ክርስትናን ለማስተማር ወደየፈለጉበት ሀገር እንደልባቸው ይሄዱ ነበር ።

ሐ) ታላቁ እስክንድር ከሮም መንግሥት መስፋፋት ቀደም ብሎ ብዙ ሀገሮችን ገዝቶ ስለ ነበር ፣ ዉሱ ጊዜና ጌታም በተወለደበት ጊዜ

የግሪክ ቋንቋ በዓለም ተስፋፍቶ ስለነበር ፣ ወንጌልን ለመስበኪያ ጠቀመ። ሐዲስ ኪዳንም የተጻፈ በጽርዕ ፣ በሮማይስጥ ፣ በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው ።

መ) ከፍልስጥኤም ውጭ ይኖሩ የነበሩት አይሁድ የፋሲካንና የጰንጠቆስጤን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው ሳለ ፣ ለሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ በተሰጠበት ቀን በጴጥሮስ ስብከት ክርስትናን የተቀበሉት ወደየመጡበት ሀገር ተመልሰው አስተማሩ ።

ሠ) ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 1፡22—32 እንደሚገልጸው ሁሉ በዚያን ጊዜ የነበረው ሕዝብ ግብረ ገብነት በጣም ተበላሽቶ ነበር ። አገልጋዮችና ሴቶች ለሰው ልጅ የሚገባውን መብት ተገፈው በሥቃይ ላይ ነበሩ ። በዚያ ሕዝቡ ለኃጢአት በተገዛበት ዘመን ጳውሎስ በገላትያ 3፡ 28 በሚያስተምረው መሠረት የክርስቶስ ተከታዮች ወንጌልን ስለሰበኩ ሕዝቡ የክርስትናን እምነት ተቀበለ ።

ረ) የክርስቲያኖች ደግ ሀብታም ፣ አሽከር ጌታ ሳይባባሉ እርስ በርስ መፋቀርና ሐዋርያት በየቦታው ይሠሩአቸው የነበሩት ታምራት የሕዝቡን አእምሮ ስለ ማረኩት ሕዝቡ ክርስትናን ተቀበለ ።

## የክርስትና ድል መንሣትና መስፋፋት

### ትልቁ ቈስጠንጢኖስ

ክርስትና ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ በሦስቱ መቶ ዘመናት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ስደቶች ቢደርሱባት ሕዝቦችን በማጽናናትና በማስተማር ተግታ ሠራች ። ይህንም የተቀደሰ እርምጃ በምታደርግበት ጊዜ የብዙ ክርስቲያኖች ንጹሕ ደም በግፍ ፈሰሰ።

የክርስቲያኖችን ጸሎት በመስማትና በግፍ የፈሰሰውን ደማቸውን በመመልከት እግዚአብሔር በትልቁ ቈስጠንጢኖስ አድሮ በ313 ዓ·ም ለክርስቲያኖች ሙሉ ነጻነትን ሰጣቸው ።

ቈስጠንጢኖስ ሰርቪያ ኒሳ (ዩጎዝላቪያ) በምትባል ቦታ ከቁንስጣና ከእሌኒ በ272 ዓ·ም ተወለደ ። በጦር ሜዳዎች ብዙ የጀግንነት ሥራዎችን ስለሠራ በሠራዊቱ ዘንድ ይወደድ ነበር ። ከአባቱ ሞት በኋላ ሕዝቡና የጦር ሠራዊቱ ንጉሠ ነገሥት አድርጎ ሾመው ። እሱም በጦር ሠራዊቱና በውጭ የነበሩትን ክርስቲያኖች በመልካም ዐይን ይመለከታቸው ነበር ።

አንድ ጊዜ ቈስጠንጢኖስ ከጠላቱ ከመክስምያኖስ ሊዋጋ ሲል እንዴት አድርጎ ጠላቱን እንደሚያሸንፍ በማሰላሰል በሐሳብ ባሕር ሲዋኝ በ312 ዓ·ም ሌሊት በራእይ "በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ታሸንፋለህ" የሚል ጽሑፍ ያለበት የሚያበራ መስቀል ከሰማይ አየ ። እሱም ይህ በራእይ ያየው መስቀል እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠው መሆኑን ተገንዝቦ በማመን ፣ በሰንደቅ ዓላማው ላይ የወርቅ መስቀል አስቀርፆ ፣ ከሠራዊቱ ፊት አስይዞ ዘመተ ። ወዲያው ሙልቪያ በተባለው በቲቤር ወንዝ ድልድይ ላይ ጠላቱን ድል ነሥቶ በጠቅላላው የሮም መንግሥት ግዛቶች ሁሉ ገዥ ሆነ ።

ክርስትናን ስለ ወደደ በ313 ዓ·ም ሚላን በተባለች ከተማ ውስጥ ለክርስትና የነጻነት ዐዋጅ ዐወጀ ። አብያተ ክርስቲያናትንም አሳነፀ ። በንዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት የተወረሰው የክርስቲያኖች ንብረትና ሀብት ፣ የአብያተ ክርስቲያናትም ንዋያተ ቅድሳት ሁሉ እንዲመለሱ አዘዘ ።

ይህም ለክርስትና ከፍ ያለ ውለታ የተደረገበት ታላቅ ጊዜ ነበር ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም የነበረው ስደት ቆመ ። ክርስትና የመንግሥቱ ሃይማኖት ስለሆነች በሚገዛቸው ሀገሮች ሁሉ እሑድ የዕረፍት ቀን እንድትሆን ወሰነ ። ይህም የዕረፍት ቀን ስለተገኘ ማንኛውም ሰው ባሮችም ጭምር ሳይቀሩ የነፍሳቸውን ድኅነት ለማግኘት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱ ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት መልካም ዕድል አጋጠማቸው ። ቈስጠንጢኖስና እናቱ እሌኒ ንግሥት ክርስትናን ተቀበሉ ። እሌኒ ከልጅዋ በፊት ተጠምቃ ብዙ የቅድስና ሥራዎችን ሠራች ። ይኸውም በ327 ዓ·ም ጌታ የተሰቀለበትን መስቀል አስቈፍራ አገኘች ። የመቃብሩንም ቦታ አግኝታ በላዩ ላይ በጌታ ትንሣኤ የሚጠራ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አሠራች ።

ቀደም ሲል የሮማ ዜጋ ያልሆነ ወንጀለኛ በስቅላት መቅጫ የነበረው መስቀል ጌታ ተሰቅሎ በደሙ ዓለምን ስላዳነበትና ቈስጠንጢኖስም ጠላቱን ድል ስለነሣበት በክርስቲያኖች ዘንድ የተከበረና የሠራዊቱ ምልክት ሆነ ።

ከናቱ ሞት በኋላ በጸና ስለታመመ በኒቆሚድያ ኤጲስ ቆጶስ በአውሳብዮስ እጅ ኒቆሚድያ በሚባል ቦታ ተጠምቆ በ337 ዓ·ም

በተወለደ በ65 ዓመቱ ዐረፈ ።

አንዳንድ ሊቃውንት ቈስጠንጢኖስ ጥምቀትን እስከ ዕለተ ሞቱ ያዘገየው በዚያን ጊዜ ጥምቀት በሕይወት ዘመን የተሠራውን ኃጢአት ሁሉ ያስተሰርያል ተብሎ ይታመን ስለነበር የሠራው ኃጢአት ሁሉ በአንድነት እንዲሰረይለት በመሻት ነበር ይላሉ ። ሌሎች ደግሞ በግዛቱ ሥር ይኖሩ የነበሩት አረማውያን በመንግሥቱ ላይ እንዳይነሡበት በመስጋት የመጠመቂያውን ጊዜ አዘገየው ይላሉ ።

## በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን መናፍቃንን ለመቃወም የተደረጉ ታላላቅ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤዎች (ሲኖዶሶች) የሚከተሉት ናቸው

### መጀመሪያው የኒቅያ ጉባኤ ።

በ3ኛው መቶ ዘመን አጋማሽ ላይ ሊብያ ውስጥ የተወለደው አርዮስ አንጾኪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት በሉሲያን መምህርነት መንፈሳዊ ትምህርቱን ከተማረና ካጠናቀቀ በኋላ ፡ የቅስና ማዕርግ ተቀብሎ እስክንድርያ ውስጥ ሲያገለግል ቈይቶ በ318 ዓ·ም "ወልድ ፍጡር ነው እንጂ አምላክ አይደለም" እያለ የክሕደት ትምህርት ማስተማር ጀምረ ። የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስ አርዮስን ይህን የተሳሳተ የክሕደት ትምህርት ማስተማሩን እንዲተው ቢመክረው እምቢ ስላለ አወገዘው ። ቈስጠንጢኖስም ነገሩን ስለሰማ እለእስክንድሮስና አርዮስ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ እንዲጨርሱት በማለት ወደ እስክንድርያ የሃይማኖት ጉዳይ አማካሪው የነበረውን አስዮስ የተባለውን መልእክተኛ ከደብዳቤ ጋር ልኮ ነበር ። ነገር ግን አርዮስ ይህንኑ የክሕደት ትምህርት ማስተማር መቀጠሉንና ጠቡም በቀላሉ የማይበርድ መሆኑን መልእክተኛው ለቈስጠንጢኖስ ስለነገረው ፡ ቈስጠንጢኖስ በ325 ዓ·ም በትንሿ እስያ ውስጥ በጥቁር ባሕር ወደብ አካባቢ በምትገኘው ኒቅያ በተባለች ከተማ ውስጥ ጉባኤ እንዲደረግ አዘዘ ። በዚህም ጉባኤ ከአርዮስ ተከታዮች በስተቀር ከየአብያተ ክርስቲያናቱ የተላኩ 318 ሊቃውንት (ጳጳሳትና ቀሳውስት) ተገኙ ። ንጉሡ ቈስጠንጢኖስም በጉባኤው ተገኝቶ ነበር ። በዚህ ጉባኤ ውስጥ እግዚአብሔር ወልድ ቀዳማዊ አምላክ ስለመሆኑ ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እየጠቀሱ አርዮስን በጥብቅ የተከራከሩ አፈ ጉባኤው

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ እለእስክንድሮስና እስክንድርያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መንፈሳዊ ትምህርቱን ያጠናቀቀው ረዳቱ ሊቀ ዲያቆን አትናቴዎስ ነበሩ ። በጉባኤው የተቀመጡት 318ቱ ሊቃውንት የሁለቱን ወገን ክርክር በጽሞና ከሰሙ በኋላ የአርዮስ ትምህርት ክሕደት መሆኑን ተገንዝበው ከነተከታዮቹ አወገዙት ። እነሱም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑንና ከአብም ጋር ትክክል መሆኑን የሚገልጽ ጸሎተ ሃይማኖትን በከፊል ፣ አምስቱ አዕማደ ምሥጢርንና ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑ ሌሎችንም ሥርዓቶች ሠሩ ።

ማሳሰቢያ ፡ የጀሖባ ምስክሮች (የመጽሐፍ ቅዱስ አጥኚዎች ፣ ጌታ ሺህ ዓመት ወደፊት ይነግሣል ባዮች ፣ ሮሳላውያን) በሚባሉና በሌሎችም ልዩ ልዩ ስሞች የሚጠሩት አሁን በዘመናችን የአርዮስን የክሕደት ትምህርትና ከክርስትና እምነት ውጭ የሆኑ ትምህርቶችን ያስተምራሉ ።

ሁለተኛው የቊስጥንጥንያ ጉባኤ ።

የቊስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ መቅዶንዮስ "መንፈስ ቅዱስ መላክ ተኛ ነው እንጂ ከአብና ከወልድ ጋር በመለኮት አንድ አይደለም ። ከአብና ከወልድ በታች ነው" የሚል የክሕደት ትምህርት አስተማረ ።

እንዲሁም በሶርያ የምትገኝ የላኦዲኪያ ኤጲስ ቆጶስ አቡሊናርዮስ "ወልድ በመለኮት ከአብ ጋር አንድ ነው ። ከማርያም ሥጋን በለበሰ ጊዜ ግን ነፍስና ዕውቀት የሌለውን ሥጋ ለበሰ ። ለለበሰውም ሥጋ መለኮት ነፍስና ዕውቀት ሆነው" የሚል የክሕደት ትምህርት አስተማረ ። በቊስጥንጥንያው ንጉሥ በቀዳማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት 150 ጳጳሳት ተሰብስበው በ381 ዓ·ም በቊስጥንጥንያ ሁለተኛውን ጉባኤ አደረጉ።

በጉባኤው ላይ ከቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎችን እያቀረቡ ሁለቱን መናፍቃን በጥብቅ የተከራከሩአቸው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚና ዙና ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ነበሩ ። የጉባኤው ተካፋዮችም የሁለቱም ትምህርት ክሕደት መሆኑን ተገንዝበው መቅዶንዮስንና አቡሊናርዮስን አወገዚቸው ። ወዲያውም የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ፡ ከአብና ከወልድ ጋር ትክክል መሆኑን የሚገልጽ ጽሑፍ በኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት በተጻፈው በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ..." የሚለውን ጨምረው ጻፉ ።

ሦስተኛው የኤፌሶን ጉባኤ ።

የቍስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ ንስጥሮስ "ወልድ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት የእግዚአብሔር አብ ልጅ ስለሆነ ከአብ ጋር ትክክል ነው ፡ ከመቤታችን ሰውነትን በነሣ ጊዜ ግን አካሉ ሁለት ነው ። አንዱ የእግዚአብሔር ልጅ ፣ አንዱ የማርያም ልጅ ነው ። አምላክ ከሰው ለመወለድ ስለማይችል እመቤታችን ማርያም የክርስቶስ እናት ናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም" የሚል የክሕደት ትምህርት ስላስተማረ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ዘመነ መንግሥት በ431 ዓ.ም በኤፌሶን 200 የሚሆኑ ጳጳሳት ተሰብስበው ጉባኤ አደረጉ ። በዚህም ጉባኤ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል መሆኑን ፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን አረጋግጠው ንስጥሮስን አወገዙት ።

ጉባኤው ከመደረጉ በፊትና በጉባኤውም ላይ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እያቀረበ ንስጥሮስን በጥብቅ የተከራከረው የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ነበር ።

ማሳሰቢያ ። የኦርየንታል (የተዋሕዶ) አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉአቸው ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን ጉባኤዎች ነው ። የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግን በሦስቱ ላይ ቀጥለን የምንመለከተውን የኬልቄዶንንና ከስድስተኛው እስከ ስምንተኛው መቶ ዘመን ድረስ የተደረጉ የልዮንን ትምህርት የሚደግፉ ፤ እንዲሁም ለጌታ ፣ ለቅዱሳን ፣ ለጻድቃን ፣ ለሰማዕታትና ለመላእክት ሥዕሎች የአምልኮ ሳይሆን የአክብሮት ስግደት መገባቱን የሚገልጹ ሌሎች ሦስት ጉባኤዎች በመጨመር ባጠቃላይ የሰባት ጉባኤዎችን ውሳኔ ትቀበላለች ። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በሰባቱ ላይ ዐሥራ አራት በመጨመር የሃያ አንድ ጉባኤዎችን ውሳኔ ትቀበላለች ።

አራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ።

በቍስጥንጥንያ ቤተ ክርስቲያን ቀሞስ የነበረው አውጣኪ "እግዚአብሔር ወልድ ከመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰውነትን በነሣ ጊዜ አምላክነቱ ሰውነቱን ስለዋጠው ረቀቀ" ብሎ የክሕደት ትምህርት ስላስተማረ በመርቅያን ዘመነ መንግሥት 650 ኤጲስ ቆጶሳት በተገኙበት በ451 ዓ.ም. ቍስጥንጥንያ ከተማ አጠገብ በምትገኘው ኬልቄዶን በተባለች ከተማ ውስጥ የተደረገው ጉባኤ አወገዘው።

ማሳሰቢያ፡፡ የአውጣኪን የክሕደት ትምህርት የኦርየንታል (የተዋ ሕዶ) አብያተ ክርስቲያናትም ይቃወሙታል፡፡ እላይ ከተጠቀሰውም በስተቀር የሮማው ሊቀ ጳጳሳት ቀዳማዊ ልዮን " ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት" የሚል ጽሑፍ (ጦማር) በኬልቄዶን ጉባኤ ለተሰበሰቡት ኤጲስ ቆጳሳት ስለላከ፣ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው ብሎ ልዮንን አወገዘው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት በእምነት ተለያዩ፡፡ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም በልዮን ትምህርት ተስማማች፡፡

የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ትምህርት የሚከተሉ የኢትዮጵያ ፣ የእስክን ድርያ፣ የሶርያ፣ የአርመን፣ የሕንድ ተዋሕዶ (ኦርየንታል) አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲ ያን ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን፣ መለኮትና ትስብእትም ያለመለየት፣ ያለመቀላቀል፣ ያለመለወጥ ስለተዋሐዱ አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ ፈቃድ፣ አንድ ግብር መሆኑን ታምናለች፡፡

ማሳሰቢያ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የቅዱስ ዲዮስቆሮስን ትምህርት የሚከተሉት አምስቱ የኦርየንታል( የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ) አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጳሳትና ቀሳውስት ከኬልቄዶን ጉባኤ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ከጥር 7 እስከ 13 ቀን 1957 ዓ.ም ድረስ ታላቅና ታሪካዊ ጉባኤ አድርገው፣ በውስጣቸው ብዙ ንኡሳን ክፍሎችን በያዙ በስድስት አንቀጾች ተነጋግረው ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

ስድስቱ አንቀጾችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

1ኛ/ ዘመናዊው ዓለምና አብያተ ክርስቲያኖቻችን፡፡

2ኛ/ በመንፈሳዊ ትምህርት ተባብሮ መሥራት፡፡

3ኛ/ ተባብሮ ወንጌላዊ ሥራን መሥራት፡፡

4ኛ/ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት፡፡

5ኛ/ በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል ያለው ነዋሪ ዝምድና የሚጸናበትን ሁኔታ የሚከታተል ድርጅት ማቋቋም፡፡

6ኛ/ ስለ ዓለም ሰላምና ፍትሕ፡፡

# በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን የተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች

ክርስትና ነጻነቷን ካገኘች በኋላ በአራተኛውና በአምስተኛው መቶ ዘመን የተነሡት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በመንፈሳዊና በፍልስፍና ትምህርት ከፍ ያለ ዕውቀት ነበራቸው። የወንጌል ትምህርት በዓለም እንዲዳረስ በማስተማርና መጻሕፍትን በመጻፍ ከደከሙት አባቶች ጥቂቶችን ከዚህ በታች እንመልከት።

1ኛ/ <u>ቅዱስ አትናቴዎስ</u>፦ በ295 ዓ·ም እስክንድርያ ውስጥ ተወልዶ የትምህርት ጊዜው ሲደርስ ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጠና ጀመር። በወጣትነቱም ዘመን ከአባ እንጦንስ ጋር መንኖ በበረሐ ጥቂት ጊዜ ቈይቶ ነበር። ቀደም ብለን በተመለከትነው በኒቅያ ጉባኤ ላይ ተገኝቶ ከአርዮስ ጋር በመከራከርና የክሕደት ትምህርቱን በማጋለጥ ረድቷል። ከሊቀ ጳጳሱ ከእለእስክንድሮስ ዕረፍት በኋላ በ328 ዓ.ም. የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ።

እሱም በዘመኑ ከነበሩት አርዮሳውያን ጋር እየተከራከረ ምእመናንን በትጋት አስተማረ። የአርዮስ ወገኖችም ለበላይ ባለሥልጣኖች በሐሰት በማሳበቅና በመክሰስ አምስት ጊዜ ያህል እንዲሰደድ አድርገዋል። ባልሠራው ወንጀል በግፍ ይህ ሁሉ ስደትና መከራ ሲደርስበት ምእመናንን ከማስተማር ተግባሩና ከቀጥተኛ እምነቱ አልተናወጸም ነበር።

በደረሱበት ስደቶች ምክንያት ጤናው ስለታወከ እስክንድርያ ውስጥ በ373 ዓ·ም ዐረፈ። በኢትዮጵያ መጀመሪያው ጳጳስ በመሆን የክርስትናን እምነት ላስፋፋው ለአቡነ ፍሬምናጦስ ( ሰላማ፣ ከሣቴ ብርሃን) የጵጵስና ማዕርግ ሰጥቶ የላከው አትናቴዎስ ነው። የአርዮስን የክሕደት ትምህርት የሚቃወሙና ለምእመናን የሚጠቅሙ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል።

2ኛ/ <u>ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ</u>፦ ቀጰዶቅያ በምትገኝ ቂሣርያ ውስጥ በ330 ዓ·ም ከሀብታም ቤተሰቦች ተወለደ። ለተወሰነ ጊዜ ጠበቃ ሆኖ ይሠራ ነበር። ባስልዮስን በመጀመሪያ የክርስትናን ትምህርት ያስተማረችው እናቱ ኤሚሊያ ስትሆን፣ ከፍ ያለ ጊዜአዊ ዝና የሚያስገኝለትን ዓለማዊ ሥራ ትቶ በተቀደሰው የክህነት ተግባር ላይ በመሰማራት

ክርስትናን ለማስፋፋት እንዲችል በመምራት ያበቃችው እኅቱ ማክሪና ናት። የትምህርት ጓደኛውም ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ነበር።

የሬቶሪክንና (የንግግርንና) የፍልስፍናን ትምህርት ቂሣርያ፣ ቊስጥንጥንያና አቴና ተምሮ ይህንኑ በማስተማር ጥቂት ጊዜ ከሠራ በኋላ ግብጽ የሚገኙትን መነኰሳትና ገዳማት በቅርብ ሆኖ ለመመልከት ሄደ። በግብጽ፡ በፍልስጥኤም ፡ በሶርያ የነበሩትን ገዳማት ጐብኝቶ ጶንዱ በምትባል ቦታ መንኲሶ በበረሐ መንኖ አምስት ዓመት ቈየ። የቂሣርያው ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስ ስላረፈ በ370 ዓ·ም· ኤጲስ ቆጶስ እንዲሆን ተመርጦ ተሾመ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምእመናንን በማስተማር፣ የአርዮሳውያንን የኑፋቄ ትምህርት በመቃወምና ልዩ ልዩ የክርስትናን ትምህርት የያዙ መጻሕፍትን በመጻፍ ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክቷል። እሱም በ379 ዓ·ም ዐረፈ።

3ኛ <u>ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ</u>፡— ቀጰዶቅያ ውስጥ እንዚናዙ አጠገብ በምትገኝ አሪዞን በምትባለው ቦታ በ328 ዓ·ም ተወለደ።

እናቱ ኖና የክርስትናን ትምህርት በትጋት ስላስተማረችው በጥቂት ጊዜ ውስጥ የክርስትናን እምነት ተቀበለ። መጀመሪያ ቂሣርያ፣ እስክንድርያና አቴና ውስጥ፣ ቀጥሎም በብዙ ሀገሮች እየዞረ ከተማረ በኋላ ወደ ሀገሩ ወደ እንዚናዙ ተመልሶ የቅስናን ማዕርግ ተቀብሎ ቤተ ክርስቲያንን ያገለግል ጀመር፣ ቀጥሎም ቅዱስ ባስልዮስ ሳሲማ ለምትባለዋ አውራጃ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾመው። እንዲሁም በ380 ዓ·ም ወደ ቊስጥንጥንያ ሄዶ ፓትርያርክ ሆኖ አስተማረ። እዚያም በሚያስተምርበት ጊዜ የአርዮሳውያንን የክሕደት ትምህርት በመቃወም የወልድን አምላክነት የሚገልጹ ከቅዱሳት መጻሕፍት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን እየጠቀሰ አንድነትንና ሦስትነትን አስፋፍቶና አብራርቶ ስላስተማረ ከሕዝቡ ነባቤ መለኮት (ቴዎጐሎስ፣ ቴዎሎጐስ) የሚል ስም ተሰጠው።

በ381 ዓ·ም ቊስጥንጥንያ ውስጥ ለተደረገችው ለሁለተኛዪቱ ጉባኤ ሊቀ መንበር ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ነበር።

በየጊዜው በትጋት ከማስተማሩም በስተቀር ለክርስቲያኖች የሚጠቅሙ ብዙ መጻሕፍት ጽፏል። እሱም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከቊስጥንጥንያ ፓትርያርክነት በፈቃዱ ተሰናብቶ ወደ ተወለደበት ቦታ ወደ አሪዞን ተመልሶ ሁል ጊዜ ይመኘው የነበረውን ጸጥ ያለ የብሕትውና ኑሮን

መኖርና መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ላይ ሳለ ባደረበት ሕመም ምክንያት በ390 ዓ·ም ዐረፈ።

4ኛ/ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፦ ቅዱስ ቄርሎስ እስክንድርያ ውስጥ በ380 ዓ·ም ተወልዶ ትምህርቱን እዚያው ተምሮ አጠናቀቀ። አባ መቃርስ ወደነበረበት ገዳም ሄዶ የብሕትውና ኑሮ በመኖር እዚያ ይሰጥ የነበረውን ትምህርትም ቀስሟል።

አጐቱ የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ እንዳረፈ በ412 ዓ·ም የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ። ቀደም ሲል አትናቴዎስ የአርዮስን የክሕደት ትምህርት በጥብቅ እንደተቃወመ ሁሉ፣ ቄርሎስም የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ንስጥሮስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት አካላት፣ ሁለት ባሕርያት አሉት፤ እመቤታችን ማርያምም የክርስቶስ እናት እንጂ የአምላክ እናት አይደለችም በማለት ያስተማረውን ኑፋቄ በጥብቅ በመቃወም ስለ አንድ ባሕርይ (ስለተዋሕዶ)፣ ስለ እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት አብራርቶ አስተምሯል።

ቄርሎስ በ430 ዓ·ም እስክንድርያ ውስጥ ጉባኤ ጠርቶ ከክሕደት ትምህርቱ አልመለስም ያለውን ንስጥሮስን አወገዘው። ወዲያውም ዐሥራ ሁለት የግዝት ዓረፍተ ነገሮችን (አንቀጾችን፣ አናሴማ) የያዘ ጽሑፍ ለንስጥሮስ ልኮ በዐሥር ቀን ውስጥ ንስሐ ገብቶ የኑፋቄ ትምህርቱን እርግፍ አድርጎ እንዲተው ቢጠይቀው አሻፈረኝ በማለቱ በ431 ዓ·ም ሁለት መቶ የሚሆኑ ጳጳሳት ተሰብስበው በሦስተኛዋ የኤፌሶን ጉባኤ ክርስቶስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል መሆኑን፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን አረጋግጠው ንስጥሮስን አወገዙት።

ቅዱስ ቄርሎስ በጻፋቸው መጻሕፍት ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ አብራርቶና አስፋፍቶ ስለገለጸ፣ እነ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በአራተኛዋ የኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ስለቀጥተኛዋ የተዋሕዶ እምነታችን ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር በማገናዘብ ለክርክራቸው መሠረት ያደረጉት የቅዱስ ቄርሎስን የመሠረተ ሃይማኖት ትምህርት ነበር።

እሱም የእስክንድርያን ቤተ ክርስቲያን በትጋት ሲያስተዳድር፣ ሲያስተምርና የተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርት የያዙ መጻሕፍት ሲጽፍ

ቈይቶ በ444 ዓ·ም ዐረፈ።

5ኛ/ <u>ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ዘእስክንድርያ፦</u> ቅዱስ ዲዮስቆሮስ እስክንድርያ ውስጥ ተወልዶ መንፈሳዊ ትምህርት እየተማረ ከአደገ በኋላ በሊቀ ዲያቆንነት ሲያገለግል ቈየ።

በ444 ዓ·ም መምህሩ ቅዱስ ቄርሎስ ሲያርፍ ወዲያው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ።

በቍስጥንጥንያው ንጉሥ በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ በዲዮስቆሮስ ሊቀ መንበርነት በ449 ዓ·ም የአውጣኪን ጉዳይ እንድትመለከት ኤፌሶን ውስጥ በተደረገችው በሁለተኛዪቱ ሲኖዶስ የሁለት ባሕርይ እምነት ደጋፊና የተዋሕዶ እምነት ተቃዋሚ የነበረውን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ፍላብያኖስን ወደ ግዞት እንዲላክ በማድረጉ፣ የፍላብያኖስ ተከታዮችና ደጋፊዎች በዲዮስቆሮስና በንጉሡ ላይ ቂም ይዘው ነበር። ሆኖም ዳግማዊ ቴዎዶስዮስ በ450 ዓ·ም ሲያርፍ በምትኩ በነገሠው በመርቅያን ትእዛዝ በ451 ዓ·ም በተደረገችው በአራተኛዪቱ በኬልቄዶን ጉባኤ ተገኝቶ ቀደም ሲል ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ ያስተማረውን የተዋሕዶ እምነት አብራርቶ አስረዳ። የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት “ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ” በማለት የሚያስተምሩትና መናፍቁ አውጣኪ “እግዚአብሔር ወልድ ከመቤታችን ከድንግል ማርያም ሰውነትን በነሣ ጊዜ አምላክነቱ ሰውነቱን ስለዋጠው ረቀቀ” ብሎ ያስተማረው የክሕደት ትምህርት መሆኑን አስረዳ። በዚህ አኳኋን ስለተዋሕዶ እምነት ሲያስረዳና ሲከራከር በኬልቄዶን ጉባኤ ላይ ከተካፈሉት ጳጳሳት አብዛኞቹ የሁለት ባሕርይን እምነት የሚቀበሉ የልዮንና የፍላብያኖስ ደጋፊዎች ስለነበሩ ተቃወሙት። በክርክሩም ወቅት ከአንዳችም ስምምነት ላይ ለመድረስ ስላልተቻለ ዲዮስቆሮስ “ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት” በማለት የሮሙ ሊቀ ጳጳስ ቀዳማዊ ልዮን በጉባኤው ለተሰበሰቡት ጳጳሳት የላከው ጽሑፍ (የልዮን ቶም፣ ጦማር) ስሕተትና ኑፋቄ ነው ብሎ ልዮንን ከነተከታዮቹ አወገዘው። አንድ የነበሩት የክርስትና እምነት ተከታዮች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተዋሕዶን እምነት የሚቀበሉና የሁለት ባሕርይን እምነት የሚከተሉ ወገኖች ሁለት ላይ ተከፈሉ። ንጉሡ መርቅያን፣ ንግሥቲቱ ብርክልያና በጉባኤው ላይ ከተካፈሉት ጳጳሳት አብዛኞቹ ሁለት ባሕርይ የሚለውን ትምህርት

ደጋፊዎች ስለነበሩ በዲዮስቆሮስ ላይ በግፍ ተነሥተው እንዲጋዝ ወሰኑበት። እሱም በትንሿ እስያ በኤጅያን ባሕር በምትገኘው ጋንግራ በተባለች ደሴት ተግዞ በመሠቃየት ላይ ሳለ በ454 ዓ.ም ዐረፈ። ከመርቅያን ሞት በኋላ የነገሠው ባሲሊኩስ የቅዱስ ዲዮስቆሮስ አጽም ወደ እስክንድርያ እንዲላክ በፈቀደው መሠረት ተወስዶ ብዙ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት ጸሎት ከተደረገ በኋላ አጽሙ እስክንድርያ በሚገኘው በቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በክብር ዐርፏል።

ባጠቃላይ በዚያን ወቅት የተፈጸመውን ሁኔታ ስንመለከት ቀደም ሲል በኒቅያ ጉባኤ በተወሰነው በመንበረ ፓትርያርኮች የክብር ደረጃ ተራ ውስጥ ያልነበረው የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ድንገት ተነሥቶ ከእስክንድርያው በክብር እበልጣለሁ ማለት ጀመረ ። በ449 ዓ.ም በተደረገችው በሁለተኛዪቱ የኤፌሶን ጉባኤ አውጣኪ ቀርቦ ሲጠየቅ እምነቱ ተዋሕዶ ነው በማለት ቃሉን በቃለ መሐላ አረጋገጠ ፤ በሲኖዶሱ አባላት ውሳኔ መሠረት ቅዱስ ዲዮስቆሮስ አውጣኪን ያንገላታውን የቍስጥንጥንያውን ፓትርያርክ ፍላብያኖስን እንዲጋዝ አደረገ ። ሆኖም ተለዋዋጭ ጠባይ የነበረው አውጣኪ ለጉባኤው አባላት በመሐላ የሰጠውን ቃሉን አፍርሶ እንደገና የክሕደት ትምህርቱን መንዛት ቢጀምርም ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በአውጣኪ የኑፋቄ ትምህርት አልተስማማም ነበር። ስለዚህ ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን ያ ሁሉ ውዝግብ የተፈጠረው ስለ ክርስቶስ ባሕርይ በተነሣው የእምነት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ፤ በዚያን ጊዜ ጠንካራ የነበረውን የእስክንድርያን መንበረ ፓትርያርክ ክብርና ደረጃ ዝቅ አድርገው የቍስጥንጥንያውን "የመናገሻ ከተማ መንበር ነው" በሚል ሽፋን ከፍ ለማድረግ ንጉሡ ፤ የሮም ፖፕና የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ ዶልተው በኬልቄዶን ጉባኤ በሃያ ስምንተኛው አንቀጽ የወሰኑት ተንኮል ጭምር ነበር ።

በኬልቄዶን ጉባኤ ወቅት ከንጉሡ ጋር በማበር ቅዱስ ዲዮስቆሮስን በመወንጀሉ ተግባር አንድ የነበሩት የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክና የሮሙ ፖፕ ቈየት ብለው እኔ እበልጥ ፤ እኔ እበልጥ በሚል የሥልጣን ሽኩቻ (ሽሚያ) ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ በመፎካከር ተለያይተው ይኖራሉ ።

6ኛ/ <u>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ</u> :- ሶርያ በምትገኘው አንጾኪያ ውስጥ በ347 ዓ.ም ተወለደ ። በሕፃንነቱ አባቱ ሲኩንዶስ ስለሞተ እናቱ አንሱሳ

ሊባንዮስ ወደተባለው አረማዊ መምህር ወስዳ የሕግና የንግግር ዘዴ (ሬቶሪክ) እንዲማር አደረገች ። እሱም ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ ጠበቃ በመሆን ጥቂት ጊዜ ሠራ ።

ቀጥሎም ተጠምቆ አንጾኪያ በነበረችው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ተማረ ። ከዚያም አባ ጳኩሚስ ቴቢያድ ውስጥ በመሠረተው ገዳም በብሕትውና ጥቂት ጊዜ ከቈየ በኋላ የዲቁና ፡ ቀጥሎም የቅስናን ማዕርግ ተቀብሎ ሕዝቡን በማስተማርና (በመስበክና) በሕመም ፡ በልዩ ልዩ ችግር ላይ የወደቁትን ድኾች ከሀብታሞች ገንዘብ እየሰበሰበ ይረዳቸው ጀመር ። ይህም የስብከትና የመመጽወት ሥራው ከአንጾኪያ ውጭ በሆኑ ሀገሮች ሁሉ ተሰማ ።

የቊስጥንጥንያው ንጉሥ ነገሥት አርቃዴዎስ የዮሐንስን ዝና ስለሰማ ያለውዴታው በ397 ዓ·ም ከአንጾኪያ ወደ ቊስጥንጥንያ ሄዶ እንዲያስተምር አደረገ ። የአንጾኪያ ሕዝብም መምህራቸውን ዮሐንስን አንሰድም በማለት ስለአወኩ ሀገረ ገዥው ሌሊት በድብቅ አውጥቶ ወደ ቊስጥንጥንያ ሰደደው ። እዚያም የቊስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ እንደ ቀድሞው ወንጌልን ማስተማር ፣ እውነትን መናገር ፡ ቀጥተኛ ፍርድን መፍረድና ለድኾች መመጽወቱን ስለቀጠለ በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅ አባት ሆነ ። ነገር ግን በእግዚአብሔር በማመን ማንንም ሳይፈራ በሰው ላይ ግፍ የሚሠሩትን ሰዎች ሁሉ ንግሥቲቱን አውዶቅስያን ሳይቀር ፣ እንዲሁም ሰነፍ የሆኑ ካህናትንም ገሠጻቸው ። በአጠቃላይ በልዩ ልዩ ወንጀልና ኃጢአት ከተዘፈቁት ምእመናንና ካህናት መካከል ምክሩን ተቀብለው በንስሐ ለመታረም ያልፈለጉት ዐይንህ ለአፈር ብለው በአንድነት እሱን ለማጥፋት ተነሡ ። ጠላቶቹ የነበሩ ጳጳሳት ከቊስጥንጥንያ ከተማ ወጣ ብላ በምትገኝ አክ በተባለች ቦታ ጉባኤ አድርገው በዮሐንስ ላይ የሐሰት ክሶችን በመደርደር ከመንበረ ፓትርያርኩ እንዲወርድ ወሰኑ ። ይህን ውሳኔና የራሳቸውን እኩይ ፍላጎት መነሻ በማድረግ በ403 ዓ·ም ንጉሡና ንግሥቲቱ የከተማው ሕዝብ አንለቅም በማለት እንዳያውካቸው ሰው ሳይሰማ በድብቅ ከከተማው ወጥቶ ወደ ጥቁር ባሕር አካባቢ እንዲሰደድ አዘዙ ። እሱም በስደት ላይ ሳለ በደረሰበት መንገላታትና ሥቃይ ምክንያት በ407 ዓ·ም ዐረፈ ። ዮሐንስ አፈወርቅ ከማስተማር ሥራው በስተቀር የክርስትናን ትምህርት የያዙ ብዙ

መጻሕፍት ጽፏል ። ለዮሐንስ "አፈወርቅ" የተባለው ስም የተሰጠው ከስብከቱ ጣዕም የተነሣ በዚያን ጊዜ ያዳምጥ ከነበረው ሕዝብ ነው ። አጽሙም በዳግማዊ ቴዎዶስዮስ ትእዛዝ በ438 ዓ.ም ወደ ቍስጥንጥንያ ተወስዶ በሐዋርያት ስም በታነጸው ቤተ ክርስቲያን በክብር ዐርፏል ። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያን አባቶች በስተቀር የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቴዎፍሎስ ፡ የኢየሩሳሌም ጳጳስ ቄርሎስ ፣ የቀጳዶቅያው ጳጳስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ፣ የሶርያው ቅዱስ ኤፍሬም ፣ የሰላሚና ጳጳስ ኤጲፋንዮስና ሌሎችም የክርስትናን ትምህርት በሰፊው በማስተማርና መንፈሳዊ ትምህርት የያዙ መጻሕፍትን በመጻፍ ደክመዋል ።

## በ4ኛው መቶ ዘመን የነበሩት አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት (ፓትርያርኮች)

በመጀመሪያው በኒቅያ ጉባኤ አንቀጽ ስድስት የሊቃነ ጳጳሳቱ ማዕርግ ከዚህ በታች እንደተጻፈው ተወስኖ ነበር ።

1ኛ/ በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የሚቀመጠው የሮም ሊቀ ጳጳስ ።

2ኛ/ በቅዱስ ማርቆስ ወንበር የሚቀመጠው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ።

3ኛ/ በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የሚቀመጠው የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ ።

4ኛ/ በቅዱስ ዮሐንስ ወንበር የሚቀመጠው የኤፌሶን ሊቀ ጳጳስ ።

በኋላ ግን የኤፌሶን ወንበር ለቈስጠንጢኖስ ሲባል ወደ ቍስጥንጥንያ ተዛወረ ። ከነዚህም በታች ሆነው የሚሠሩ በብዙ ሀገሮች ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ተሹመው ነበር ።

የሮማውና የቍስጥንጥንያው የመናገሻ ከተማዎች ሊቃነ ጳጳሳት ስለነበሩ በመካከላቸው የነበረው የማዕርግ ፉክክር እንዲቆም በማለት በሥልጣን እኩል ሆነው በሽምግልናና በአክብሮት የሮሙ 1ኛ ፤ የቍስጥንጥንያው 2ኛ ፤ እንዲሆኑ በቍስጥንጥንያው ጉባኤ አንቀጽ ሦስትና በኬልቄዶን ጉባኤ አንቀጽ ሃያ ስምንት ተወሰነ ። እንዲሁም በኬልቄዶን ጉባኤ በኢየሩሳሌም ወንበር የሚቀመጠው ሊቀ ጳጳስ 5ኛ እንዲሆን ተወሰነ ።

በጉባኤው የተወሰነውን ባለማክበር የሮሙ ፖፕና የቍስጥንጥንያው ፓትርያርክ እኔ እበልጥ ፣ እኔ እበልጥ በመባባል እስከ ዛሬ ድረስ

ሲፎካከሩ ይታያሉ ። የቊስጥንጥንያውም ፓትርያርክ የዓለም ፓትርያርክ በሚል ስም ይጠራ ጀመር ።

## በኦርየንታል (በተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ ፣ በግሪክ ኦርቶዶክስ ፣ በካቶሊክና በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ካሉት የሃይማኖትና የሥርዓት ልዩነቶች ጥቂቶቹ (ዋና ዋናዎቹ)

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው በክሕደት ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አባልነታቸው በጉባኤ ተወግዘው ከተወገዱት ከአርዮስ ፣ ከመቅዶንዮስ ፣ ከንስጥሮስና ከተከታዮቻቸው በስተቀር እስከ አራተኛው የኬልቄዶን ጉባኤ ድረስ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የእምነት ልዩነት አልነበረም ። ከኬልቄዶን ጉባኤ ጀምሮ ግን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚከተሉት ልዩነቶች ተከስተዋል ። እነሱም:-

1ኛ/ የካቶሊክና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ለኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ባሕርያት አሉት ሲሉ ፣ የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በተዋሕዶ አንድ ባሕርይ ነው ይላሉ ።

2ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድም ሠረፀ ስትል ፣ የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መንፈስ ቅዱስ ከአብ ብቻ ሠረፀ ይላሉ ።

3ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሰዎች ስለሠሩት ኃጢአት በመጸጸት ንስሐ ገብተው ሳይፈጽሙት በድንገት ሲሞቱ ፣ በመንግሥተ ሰማያትና በገሃነመ እሳት መካከል ልዩ የሆነ ቦታ (መካነ ንስሐ ፣ ፐርጋቶሪ) ስላለ ፣ ነፍሶቻቸው ወደዚያ ሄደው ከኃጢአታቸው እስኪነጹ ድረስ መከራ እየተቀበሉ ቈይተው ኋላ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ በማለት የምታስተምረውን ትምህርት የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉትም ።

4ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሮም ፖፕ የክርስቶስ እንደራሴና የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በላይ ስለሆነ በመንበሩ ተቀምጦ (ተሠይሞ) በሚወስነው ሁሉ አይሳሳትም ብላ በ1870 ዓ·ም በቫቲካን አንድ ጉባኤ የወሰነችውን ፣ የኦርየንታልና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጉባኤ ተሰብስበው በተገኙበት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተወሰነውና ለወደፊትም የሚወሰነው ውሳኔ (ድንጋጌ)

ነው የማይሳሳት በማለት የአንድ ሰው የፖፑን አለመሳሳት አይቀበሉም ። ፖፑ የሁሉ የበላይ ነው በማለት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረ ውንም ይቃወማሉ ።

5ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን አጥምቃ ሜሮን የምትቀባ ቸው ነፍስ ካወቁ በኋላ ነው ። የአርየንታልና የግሪክ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ሕፃናትን አጥምቀው ወዲያው ሜሮን ይቀቧቸዋል ።

6ኛ/ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ለቀዳስያን ካህናት ሥጋ ወደሙን ስትሰጥ ለምእመናን ሥጋውን ብቻ አቀብላ ደሙን አታቀብልም ነበር። ነገር ግን በቫቲካን ሁለት ጉባኤ ለምእመናንም ሥጋ ወደሙ እንዲሰጣ ቸው ተፈቅዷል ። የአርየንታልና የግሪክ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያ ናት ግን ለካህናትና ለምእመናን ሥጋ ወደሙን ይሰጣሉ ። ከዚህም ጋር የተዋሕዶ አርቶዶክሳውያን የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው ፡ መለኮት የተዋሐደው ነው ስንል ፡ ካቶሊካውያን ግን ነፍስ ያለው መለኮት የተዋሐደው ነው ይላሉ ።

እንዲሁም በተለያዩ ሀገሮች የሚኖሩ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች እንደ ልደትና ፋሲካ የመሳሰሉትን በዓላት የምዕራብ ሀገሮች በሚያከብሩበት ቀን ሳይሆን የሚኖሩበት ሀገር ክርስቲያኖች በሚያከብሩበት ቀን አብረው እንዲያከብሩ ተፈቅዶላቸዋል ።

7ኛ/ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናት ቅዱስ ቍርባንን የሚቀበሉ ነፍስ ዐውቀው ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ሲሆን ፡ በአርየንታልና በግሪክ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን ከተጠመቁና ሜሮን ከተቀቡ በኋላ ወዲያው ይቈርባሉ ።

8ኛ/ በ306 ዓ·ም እስፖኝ ውስጥ በተደረገችው በኤልቪራ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህናት በመላ ሚስት አያገቡም። የአርየንታልና የግሪክ አርቶዶክስ ካህናት ግን ከጳጳሳት በስተቀር ቀሳውስትና ዲያቆናት ከፈለጉ አንዳንድ ሚስት አግብተው ሥልጣነ ክህነት ተቀብለው ሊያገለግሉ ይችላሉ ።

9ኛ/ የካቶሊክ ካህናት ጽሕማቸውን ሲላጩ ፡ የአርየንታልና የግሪክ አርቶዶክስ ካህናት ግን ያሳድጉታል ።

10ኛ/ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አብዛኛውን ጊዜ ከሥዕል በተጨ ማሪ ለጌታ ፡ ለመቤታችን ፡ ለጻድቃንና ለሰማዕታት መታሰቢያ የድንጋይ ሐውልት ሲቀረፅላቸው ፡ በአርየንታልና በግሪክ አርቶዶክስ አብያተ

ክርስቲያናት ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በሥዕል ይሣላሉ ።

11ኛ/ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚፈጸሙት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ፣ በካህናት ልብስ ፣ በቋንቋና እነዚህን በመሳሰሉት ሁሉ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሥርዓት ይለያያል ።

12ኛ/ በ16ኛው መቶ ዘመን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተለዩት ፕሮቴስታንቶች የፖፑን የበላይነትና አይሳሳትም የሚለውን ትምህርት አይቀበሉም ። የፕሮቴስታንቶች ሃይማኖት መገኛ ስድሳ ስድስቱን መጻሕፍት የያዘው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ። ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ እንደመሰለው ሊተረጉም ይችላል ። በዚህም ዐይነት መንገድ ፕሮቴስታንቶች እያንዳንዳቸው መጽሐፍ ቅዱስን እንደ መሰላቸው ሲተረጉሙ በሐሳብ በመለያየታቸው ምክንያት በየጊዜው በእምነት እርስ በእርሳቸው ተለያዩ ።

ምንም እንኳ ማዕርገ ክህነት ከጌታ ለሐዋርያት የተሰጠ ፣ ከሐዋርያትም ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ መሆኑን በመቃወም እንደ ምሥጢር ባይቈጥሩትም ከሦስቱ ማዕርገ ክህነት ቅስናንና ዲቁናን ስሙን ብቻ ይቀበላሉ ። ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ግብረ ገብነትን የተመረከዘ መልካም ኑሮ ከኖረና በቂ የመንፈሳዊ ትምህርት ዕውቀት ካለው በአንብሮተ እድ ባይሾምም የካህናትን ሥራ ሊሠራ ይችላል ይላሉ ።

ከፕሮቴስታንቶች የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሦስቱን ማዕርገ ክህነት እንደ ምሥጢር ቈጥራ ትቀበላለች ። ፕሮቴስታንቶች ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ጸጋ የሚሰጥ በጥምቀትና በቍርባን ብቻ ነው ይላሉ ። ካህኑ በሚጸልይበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ አይሆንም ይላሉ ። በወይኑም ውኃ አይጨምሩበትም ። ሕፃናትን አጥምቀው ቅዱስ ቍርባንን የሚሰጡአቸው ነፍስ ካወቁ በኋላ ነው ። ባፕቲስት የሚባሉት በሕፃንነት የሚፈጸመውን ጥምቀት ይቃወማሉ ። አናባፕቲስት የተባሉት ደግሞ የሕፃናትን ጥምቀት በመቃወም የተጠመቁትን እንደገና ያጠምቃሉ ። ከፕሮቴስታንቶች ጥቂቶቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ በስተቀር ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ የሏቸውም ።

ንስሐን እንደ ምሥጢር ሳይቈጥሩ የሰውን ጠባይ ያሻሽላል ፣ ሰዎችን ለማጽናናት ይችላል በማለት ቢቀበሉትም ቅሉ ፣ ኃጢአትን

ለንስሐ አባት መናገር አያስፈልግም አሉ ። ንስሐ ገብቶ ሳይፈጽመው ድንገት የሚሞተው ሰው ነፍሱ በንስሐ ቦታ ነጽታ ወደ መንግሥት ሰማያት ትገባለች የሚለውን የካቶሊኮችን እምነት አይቀበሉትም ።

ከበዓላት ቀኖችም እሑድን ፣ ልደትን ፣ ጥምቀትን ፣ ትንሣኤንና ዕርገትን ብቻ ተቀበሉ ።

ለጌታ ሁለት ባሕርያት አሉት ብለው ያምናሉ ። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሠረፀ ይላሉ ።

በተለይ ካልቪን እግዚአብሔር የተወሰኑ ነፍሳትን እንዲድኑ ፣ የቀሩት እንዲጠፉ ወስኗል ብሎ አስተማረ ። እዝቪንግልም ጾምን በፍጹም አስወገደ ። በየጊዜው የተነሡ የፕሮቴስታንት መሪዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና እነዚህን የመሳሰሉ ትምህርቶችን አስተማሩ ።

በዚህ አኳኋን የሉተር ፣ የእዝቪንግልና የካልቪን ተከታዮች ከጥንት ጀምረው ክርስትናን የተቀበሉ የኦርየንታል (የተዋሕዶ) ኦርቶዶክስ ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ያመኑባቸውን እምነቶች ተቃወሙ ። ይኸውም የሃይማኖት ትምህርት መገኛዎች መጽሐፍ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፉአቸው መጻሕፍት ፣ በየጊዜው የተደረጉት ጉባኤዎች ድንጋጌ ሲሆኑ ፣ ፕሮቴስታንቶች ግን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ተቀብለው የቀሩትን አልተቀበሉም ። ከነዚህም በስተቀር ምንኵስናን ፣ ግዕርገ ክህነትንና የጻድቃንን ማማለድ ተቃወሙ። እንዲሁም የጻድቃንና የሰማዕታት ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዳይገኙና የጸጋና የአክብሮት ስግደት እንዳይደረግላቸው ተቃወሙ ። በዚህ አኳኋን በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ጌጦችና ሥዕሎች እንዳይገኙ አደረጉ ። ከሰባቱ ሥርዓታተ ቤተ ክርስቲያን አምስቱንና እነዚህን የመሳሰሉትን ትምህርቶች አልተቀበሉም ።

የኦርየንታል ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ቄሱ በሚጸልይበት ጊዜ ኅብስቱና ወይኑ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ደመ አምላክ ይሆናል ሲሉ ፣ ፕሮቴስታንቶች አይለወጥም ይላሉ ። እንዲሁም የኦርየንታል ፣ የግሪክ ኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ድኅነት የሚገኘው ከእምነትና ከደጋግ ሥራዎች ነው ሲሉ (ያዕ·2፥ 14–26፤ ማቴ·7፥21) ፣ ፕሮቴስታንቶች ግን ድኅነት የሚገኘው ከእምነት ብቻ ነው ይላሉ ።

<u>ማሳሰቢያ</u> ። ፕሮቴስታንቶች በየጊዜው እርስ በእርሳቸው በሃይማ

ኖት በመለያየታቸው ምክንያት የእምነታቸው ዐይነት ብዙ ነው ። በተለይ በአሜሪካን ሀገር ብቻ በእምነት ተለያይተው የየግል እምነታቸውን ይዘው የሚገኙት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት (ዴኖሚኔሽን) ቊጥር ከሁለት መቶ ስልሳ በላይ ነው ። ስለዚህ እላይ የተዘረዘሩት እምነት ነክ ትምህርቶች ቀደምትና ዋና ዋና በሆኑት የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚሰጡ ትምህርቶች ናቸው እንጂ የሁሉንም አያጠቃልሉም ።